# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

83ኛ ዓመት ቁጥር 058 ጥቅምት 28 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# አይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ

## ግንባታ አጠቃላይ ሥራው 82 በመቶ ደርሷል

### - የ32 ተርባይኖች ገጠማ ተጠናቋል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የአይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ግንባታ አጠቃላይ የግንባታ ሥራው 82 በመቶ መድረሱን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አስታወቀ፡፡ የ32 ተርባይኖችና ጄኔሬተር ገጠማ መጠናቀቁም ተገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የአይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ግንባታ የ32 ተርባይኖች ጀኔሬተር ገጠማ በመጠናቀቁ አጠቃላይ ሥራው 82 በመቶ ደርሷል።

እንደ አቶ ሞገስ ገለጻ፤ የአይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ግንባታ ሙሉ ለሙሉ ባይጠናቀቅም ባለው አቅም የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲያመነጭ ተደርጓል።

በፕሮጀክቱ ከተገጠሙት 32 ተርባይኖች መካከል በ16 ተርባይኖች አማካኝነት 40 ሜጋ ዋት ኃይል ማመንጨት መጀመሩን አመልክተው፤ የቀሪዎቹ የፍተሻ ሙከራ ሥራዎቻቸው ሲጠናቀቁ ሙሉ በሙሉ ኃይል ማመንጨት እንደሚጀምሩ ገልጸዋል፡፡

ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ በአጠቃላይ 48 ተርባይኖች እንደሚገጠሙ አስረድተው፤ ቀሪ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ ሰፊ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

ፕሮጀክቱ በ257 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወጪ የሚገነባ መሆኑን አስታውቀው፤ የግንባታ ወጪውን 85 በመቶ የቻይናው ኤግዚም ባንክ ቀሪውን 15 በመቶ ደግሞ በኢትዮጵያ መንግሥት እንደሚሸፈን አቶ ሞገስ አመልክተዋል፡፡

በሶማሌ ክልል እየተገነባ የሚገኘው የአይሻ 2 የንፋስ

አይሻ 2 የንፋስ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ‹‹ቻይና ከኢትዮጵያ ጋር በቱሪዝም ዘርፍ ይበልጥ ለመሥራት ቁርጠኛ ናት››

- ሚስተር ሺን ኪንሚን
በኢትዮጵያ የቻይና ኤምባሲ ምክትል ኃላፊ

ገጽ 4

## አውደርዕዩ የዘርፉን ዕምቅ አቅም በማስተዋወቅ ረገድ ውጤታማ ሆኗል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ሀገር አቀፍ የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ አውደርዕይ የዘርፉን ዕምቅ አቅም በማስተዋወቅ ረገድ ውጤታማ መሆኑን የቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ። አውደርዕዩን ከ154 ሺህ በላይ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገራት ቱሪስቶች ጎብኝተውታል።

ከመስከረም 29 እስከ ጥቅምት 28 ቀን 2016 ዓ.ም በሳይንስ ሙዚየም ሲካሄድ የቆየው ሀገር አቀፍ የቱሪዝም ኤግዚቢሽንና ሆስፒታሊቲ አውደርዕይ የመዝጊያ ፕሮግራም ትናንት ተካሂዷል፡፡

በወቅቱ የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ፤ አውደርዕዩ ዘርፉን ለማሳደግ ምቹ አጋጣሚ የተፈጠረበት ነው ብለዋል። መድረኩ ቱሪዝሙን በማነቃቃትና መዳረሻዎችን በማስተዋወቅ ረገድ ጉልህ ሚና እንደነበረው አንስተዋል።


ከአውደርዕዩ የተፈለገውን ውጤት ማግኘት ተችሏል ያሉት

አውደርዕዩ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - አዩብ ተፈሪ

አቶ ስለሺ ግርማ



## የነዳጅ ድጎማ

### ያለአግባብ በተጠቀሙ ሁለት ሺህ 102 አሽከርካሪዎች ላይ ርምጃ ተወሰደ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት አገልግሎት ሳይሰጡ የነዳጅ ድጎማ ያለ አግባብ የተጠቀሙ ሁለት ሺህ 102 አሽከርካሪዎች ገንዘቡን እንዲመልሱ መደረጉን የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር የብሔራዊ የታለመለት ነዳጅ ድጎማ ፕሮጀክት አስተባባሪ አቶ ሰልማን መሀመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት

የነዳጅ ድጎማ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል
















# በክልሉ የአንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር ተኪ ምርቶችን ለማምረት ታቅዷል



አቶ ተፈሪ ታረቀኝ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር የሚያወጡ ተኪ ምርቶችን ለማምረት መታቀዱን የአማራ ክልል ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ አስታወቀ፡፡

በአማራ ክልል የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ከተጀመረ ጀምሮ በዘርፉ በርካታ ውጤቶችን ማስገኘት እንደቻለ ተገልጿል፡፡

የቢሮው ምክትል ኃላፊ አቶ ተፈሪ ታረቀኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ አዳዲስ የሀገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስተሮችን መሳብ፣ የተኪ ምርቶችን ምርት ማሳደግ፣ ነባር ኢንዱስትሪዎች ላይ ያሉ ማነቆዎችን መፍታት የሚሉ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡

በንቅናቄው በ2015 በጀት ዓመት በአጠቃላይ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ በተኪ ምርት በማዘጋጀት የውጭ ምንዛሬን ማዳን የተቻለ ሲሆን፤ በ2016 በጀት ዓመት በተኪ ምርቶች አማካኝነት ከአንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ለማዳን መታቀዱን አስታውቀዋል፡፡

ከጨርቃጨርቅ፣ ከማኑፋክቸሪንግና ከተለያዩ የኢንዱስትሪ ዘርፎች የሚገኙ ተኪ ምርቶችን ለገበያ በማቅረብ ገቢ ለማግኘት እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

በተያዘው በጀት ዓመት ከአምስት ሺህ በላይ ለሆኑ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ቢታቀድም በክልሉ ባጋጠመው የጸጥታ መደፍረስ ምክንያት በሩብ ዓመቱ የኢንቨስትመንት ፍሰት መዳከሙን አንስተዋል።

የተፈጠረውን የሰላም መደፍረስ ከማህበረሰቡና ከፀጥታ አካሉ ጋር በመረባረብ በመፍታት በሩብ ዓመቱ የባከነውን ጊዜ ለማካካስና የተሻለ አፈጻጸም ለማስመዝገብ በትኩረት እንደሚሠራ አመላክተዋል፡፡

የክልሉ መንግስት የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄን በሙሉ አቅም ለማገዝ፣ ችግር ያለባቸው መመሪያዎችንና አሠራሮችን ለማሻሻልና በቅንጅት ለመሥራት የሚያግዝ ውሳኔ አሳልፏል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄን ማህበረሰቡ ድረስ ለማውረድ ትኩረት ተደርጓል ያሉት አቶ ተፈሪ፤ ሁሉም ማህበረሰብ የድርሻውን እንዲወጣ የተለያዩ አደረጃጀቶችን የመፍጠርና በጀት የማቅረብ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በዘርፉ ከሚስተዋሉት ማነቆዎች መካከል የመሬት ዝግጅት አንዱ ነው ያሉት አቶ ተፈሪ፤ መሬት በክላስተር ከተዘጋጀ በኋላ ባለሀብቱ ለአርሶአደሩ ተገቢውን ካሳ ከፍሎ እንዲያለማ የሚያግዝ መመሪያ ተዘጋጅቶ ወደትግበራ መግባቱን አስረድተዋል፡፡

የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ሌላኛው የዘርፉ ማነቆ መሆኑን ጠቁመው፤ በርካታ የኢንዱስትሪ መንደሮች የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያገኙት ለነዋሪዎች ተብሎ ከተዘረጋ መስመር በመሆኑ ችግር መፈጠሩን ገልጸዋል።

ችግሩን ለመፍታት ከሰብስቴሽን ወደ ኢንዱስትሪ መንደሮች እራሱን በቻለ መስመር ኃይል እንዲያገኙ ለማድረግ የክልሉ መንግሥት ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በ2015 በጀት ዓመት ከአምስት ሺህ 700 በላይ አዳዲስ ባለሀብቶች ወደክልሉ መጥተው የኢንቨስትመንት ፈቃድ መውሰዳቸውን ተናግረው፤ 578 ባለሀብቶች 780 ሄክታር መሬት ተቀብለው ወደ ሥራ መግባታቸውን አስታውሰዋል፡፡

28 ሺህ ለሚደርሱ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል መፍጠር የቻሉ 255 አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን ወደሥራ ከማስገባት በተጨማሪም በተለያዩ ማክንያቶች ሥራ ያቆሙና የማምረት አቅማቸው ዝቅተኛ የነበሩ 149 ፕሮጀክቶች በሙሉ አቅም ወደሥራ እንዲገቡ መደረጉን ገልጸዋል።

# የውሃ ሀብት ልማትንና አጠቃቀምን በማዘመን ከኢኮኖሚ ችግሮች ለመውጣት ትኩረት ያሻል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የውሃ ሀብት ልማትንና አጠቃቀምን በማዘመን ከኢኮኖሚ ችግሮቻችን ለመላቀቅ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የውሃ ምህንድስና መምህርና ተመራማሪ በፕሮፌሰር መኮንን አያና አስታወቁ፡፡

በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የውሃ ምህንድስና መምህርና ተመራማሪ በፕሮፌሰር መኮንን አያና በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት ዝናብ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህን በዝናብ ጥገኛ የሆነ የውሃ ሀብት አጠቃቀምን በማዘመን ከኢኮኖሚ ችግሮች ለመውጣት ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

የኢትዮጵያ የውሃ ሀብትና የምግብ ሰብል የማምረት አቅማችን ዝናብ ላይ የተመሠረተ ነው ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ ይህን በዝናብ ላይ የተመሠረተ በውሃ ሀብታችን በልማትና አጠቃቀሙን በማዘመን ከብዙ ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻችን መውጣት ይገባል ብለዋል፡፡

ውሃን በትክክል የማልማት አቅም በመገንባት ከብዙ ችግሮች መላቀቅ የሚቻል መሆኑን ተገንዝቦ በልዩ ትኩረት መሥራት እንደሚያስፈልግ አመልክተው፤ በውሃ ዙሪያ የሚሠሩ ተቋማትን እንደገና በማዋቀር አቅምን መገንባት አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ችግሮች የሚነሱት ውሃን በአግባቡ ማልማት ካለመቻላችን ጋር ተያይዞ መሆኑን ገልጸው፤ የመጠጥ ውሃና የኤሌክትሪክ ኃይል በሚፈለገው ልክ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ ያልተቻለው ውሃ አልምቶ አለመጠቀማችንና አጠቃቀማችን ማዘመን ለመቻላችን መሆኑን ገልጸዋል፡፡

እንደ ፕሮፌሰር መኮንን ማብራሪያ፤ በዘመናዊ አኗኗር ውስጥ ውሃ ለኤሌክትሪክ ኃይልን በማመንጨት ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ የተሻለ ሕይወትን ለመኖር ውሃን ማልማት ትኩረት ያሻዋል፡፡

የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ በሄደ ቁጥር የውሃ ፍላጎትም እያደገ ይሄዳል ያሉት ፕሮፌሰር መኮንን ፤ የውሃ አጠቃቀምን ማዘመን ለችግሮቻችን መፍትሔ መፈለጊያ መንገድ መሆኑን መገንዘብ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥሩ እየጨመረ በመምጣቱና አየር ንብረት ለውጥ በሚያስከትለው ድርቅ ምክንያት ያለን ውሃ በቂ ነው ማለት እንደማይቻል ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ናት የሚለው አገላለጽ የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት ከከፍታ ቦታ ወደ ዝቅተኛ ቦታ በመፍሰስ ድንበር ተሻግረው የሚወጡ ወንዞች መኖራቸው ለማመላከት መሆኑን ጠቁመው፤ ይህን አባባል በተሳሳተ መንገድ በመተርጎም ኢትዮጵያ የተትረፈረፈ የውሃ ሀብት እንዳላት መገንዘብ ተገቢ አይደለም ነው ያሉት፡፡

ወንዞቻችን በዓመት ውስጥ ከአራት ወራት ውጪ የተቀሩትን ስምንት ወራት በሙሉ ዝቅተኛ የውሃ አቅም ያላቸው መሆናቸውን ገልጸው፤ ይህን የውሃ ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የተለያዩ ግድቦችን መገንባት እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል፡፡

የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ለብዙ ዘመናት ከኢትዮጵያ ተነስተው ድንበር ተሻግረው በሚሄዱ ወንዞች እንደፈለጉት የሚጠቀሙትን ልምድ መቀየር አይፈልጉም ያሉት ፕሮፌሰር መኮንን፤ ኢትዮጵያ የሕዝቦቿን ኑሮ ለማሻሻል ያላትን የውሃ ሀብት በፍትሃዊነት እንደምትጠቀም ነው የገለጹት፡፡

ኢትዮጵያ የጋራ ተጠቃሚነትን በጽኑ የምታምን በመሆኗ ከሌሎችም ሀገራት ጋር በጥሩ ጉርብትና በፍትሀዊነት የመጠቀም ፍላጎት አላት፡፡ ይህንንም እያረጋገጠች ትገኛለች ብለዋል፡፡



አቶ ድዳ ድሪባ



አቶ ጥበቡ አሰፋ

# በመዲናዋ የአየር ጥራትን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ 10 ዘመናዊ መሣሪያዎች ተገጥመዋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የመዲናዋን የአየር ጥራት ለመቆጣጠር የሚያስችሉ 10 ዘመናዊ መሣሪያዎች መገጠማቸውን የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አስታወቀ። በአፍሪካ ከተሞች ያለውን የአየር ጥራት ለማሻሻል የሚያግዝ ሥልጠና ትናንት በአዲስ አበባ ተካሂዷል።

ሥልጠናውን የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን 40 ከተሞች ካዋቀሩት c40 ከተሰኘው ጥምረት ጋር በመተባበር ያዘጋጀው ሲሆን ይህም ከትናንት ጀምሮ እስከ ጥቅምት 29 ድረስ የሚካሄድ ይሆናል።

የአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ድዳ ድሪባ በሥልጠናው ወቅት እንደተናገሩት፤ በመዲናዋ የአየር ጥራት ለመቆጣጠር የሚያስችሉ 10 ዘመናዊ መሣሪያዎች ተገጥመዋል፡፡

ይህ መደረጉ ለአየር መበከል አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ጋዞችና ብናኞች ጋር ተያይዘው የሚመጡ የጤና ችግሮችን ለመቀነስ ያስችላል ።

የአየር ጥራትን ለመጠበቅ የአፍሪካ ከተሞች ለንፁህ አየር መርሃ ግብር ተግባራዊ እየተደረገ ነው ያሉት ኃላፊው፤ መርሃ ግብሩ በ 11 የአፍሪካ ከተሞች ያለውን የአየር ጥራትን ለማሻሻል የሚያግዝ እንደሆነ ገልጸዋል።

የአፍሪካ ከተሞች ተገቢውን የአየር ጥራት መሣሪያ በመትከልና ልኬት በማድረግ መረጃን መሰብሰብ፤ መከታተልና የማሻሻል ሥራ መሥራት እንዲችሉ ሥልጠናው መዘጋጀቱን ጠቅሰዋል፡፡

በሥልጠናው አዲስ አበባን ጨምሮ፣ ናይሮቢ፣ ሌጎስ፣ ፍሪታውን፣ ጆሃንስበርግ፣ ደርባን፣ ፕሪቶሪያ እና ሌሎች የወጭ ሀገራት ተሳታፊ ሆነዋል ብለዋል።

በC40 የአፍሪካ የአየር ጥራት ቴክኒካል አማካሪ አቶ ጥበቡ አሰፋ በበኩላቸው፤ ሥልጠናው በዓለም የጤና ድርጅት በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ሀገራት የአየር ጥራት ደረጃ (ስታንዳርድ) እንደሚያዘጋጁ ጠቅሰዋል።

የአየር ጥራት ደረጃ መዘጋጀቱ ለጤና ተስማሚ የሆነ አየር ጥራት እንዲኖር እንደሚያስችል ተናግረዋል።

ለአየር መበከል አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ጋዞችና ብናኞች ጋር ተያይዘው የሚመጡ የጤና ችግሮችን ለመቀነስ የc40 ጥምረት በርካታ ሥራዎችን እየሠራ ነው ያሉት አቶ ጥበቡ፤ የአፍሪካ ከተሞች ለንፁህ አየር መርሃ ግብር የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች እየተሰጠ መሆኑን ገልጸዋል።

የአየር ጥራት መረጃ በተለይ በተገቢው ጊዜና ቦታ መረጃ መስጠት የአየር ብክለትን ተጋላጭነትን ለመቀነስ ወሳኝ ሚና አለው ብለዋል፡፡



አቶ ገብረመስቀል ጫላ

# ሚኒስቴሩ ነባርም ሆኑ አዲስ ነጋዴዎች ፈቃድ እንዲወስዱ አሳሰበ

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በጫት የወጪ ንግድ ሥራ ፈቃድ አውጥተው የሚንቀሳቀሱ ነጋዴዎችም ሆኑ ወደ ንግዱ መግባት የሚፈልጉ ነጋዴዎች ሚኒስቴሩ ባዘጋጀው አዲስ የቅድመ ፈቃድ ብቃት መስፈርት መሠረት እስከ ህዳር 15 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ፈቃድ እንዲወስዱ አሳሰበ፡፡

ኢትዮጵያ ከጫት ምርት የምታገኘው የውጭ ምንዛሪ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱን በመግለጫው ያስታወቀው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ፤ ንግድ ፈቃድ ያላቸው ነጋዴዎች ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ በመላካቸው፣ የንግድ ሥራ ፈቃድን ለሌላ ወገን በማስተላለፍ ሥራ ላይ መሳተፋቸውና፣ የኮንትሮባንድ ንግድ ከልክ በላይ መስፋፋት የጫት ወጪ ንግድ ገቢ በእጅጉ እንዲቀንስ ምክንያት መሆናቸውን ገልጿል፡፡

ይህም በጫት ምርት ሥራ ላይ የሚገኙትን አርሶ አደሮች ከምርቱ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም በማጣት ለከፍተኛ ጉዳት እየዳረገ እንደሆነም አመላክቷል፡፡

በጫት ወጪ ንግድ ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፈና ኢትዮጵያ ከንግዱ ማግኘት የሚገባትን ገቢ ለማሳደግ አዲስ አቅጣጫ ማስቀመጥና ርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ማግኘቱን መግለጫውን የሰጡት ሚኒስትሩ ገብረመስቀል ጫላ እንዳስታወቁት፤ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ነባር ነጋዴዎች በዳግም ምዝገባ ተካተው የንግድ ሥራቸውን እንዲያከናውኑና መመዘኛውን የሚያሟሉ አዲስ ነጋዴዎች በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ፈቃድ ማውጣት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡

በጫት ወጪ ንግድ ፈቃድ አውጥተው የሚንቀሳቀሱ ነጋዴዎችና ሀገር ተገቢ ጥቅም እንዲያገኙ የሀገር ውስጥ ጫት ዋጋ ከጎረቤት ሀገራት ዋጋ አንጻር ምን ይመስላል የሚለውን ጥናት እያደረገ እንደሆነ የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ የኮንትሮባንድ ንግድን ለመከላከል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ክልሎች፣ የፌዴራል መሥሪያ ቤቶችና ኃላፊዎች ጋር በከፍተኛ ጥምረት እየሠራ እንዳለ ጠቁመዋል፡፡

የኮንትሮባንድ ንግድን በማጥራት ሥራ በተለዩ መስመሮች ላይ የማያዳግም ርምጃ እንደሚወስድም አሳውቀዋል፡፡

በጫት ምርት ሕይወቱን የሚመራው አርሶ አደር የምርቱ ዋነኛ ተጠቃሚ እንዲሆንና ከጫት ወጪ ምርት ኢትዮጵያ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ እንድታገኝ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ የገለፁት ሚኒስትሩ፤ ከትናንት ጥቅምት 27 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚወሰዱ ርምጃዎችን የንግዱ ማኅበረሰብና የሚመለከታቸው ሁሉ ሊያውቁት እንደሚገባም አሳስቧል፡፡

# በኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሁለት ሺህ 802 ጨረታዎች ወጥተዋል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ሁለት ሺህ 802 ጨረታዎች መውጣታቸውን የግዢና ንብረት ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡ 161 የፌዴራል ተቋማት በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ግዢ ለመፈጸም ዕቅድ ማቅረባቸውም ተጠቁሟል፡፡

የግዢና ንብረት ባለሥልጣን ኤሌክትሮኒክስ ግዢ ላይ ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር ትናንት ውይይት አካሂዷል፡፡

በውይይቱ ላይ የተገኙት የግዢና ንብረት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀጂ ኢብሳ እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት ዓመት የፌዴራል መሥሪያ ቤቶች ግዢ ሙሉ ለሙሉ በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ብቻ ይፈጸማል። በዚህ መነሻነትም በኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሁለት ሺህ 802 ጨረታዎች ወጥተዋል፡፡

ከ 169 የፌዴራል ተቋማት 161 ተቋማት በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ግዢ ለመፈጸም ዕቅድ ማቅረባቸውን ጠቁመው፤ ቀሪዎቹ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሥርዓቱን እንደሚቀላቀሉ ጠቁመዋል፡፡

የኤሌክትሮኒክስ ግዢው በአካል መገናኘት ሳያስፈልግ የሚፈጸም በመሆኑ በግዢ ሥርዓቱ ሲያጋጥም የነበረውን ሌብነት እንደሚያስቀር አመልክተው፤ ጊዜና ገንዘብ ቆጣቢ እንደሆነም ተናግረዋል።

በኤሌክትሮኒክስ ግብይቱ እውነተኛ ዋጋና ጥራት የያዘ ተጫራች አሸናፊ የሚሆንበት መሆኑን የተናገሩት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ለተጫራቾችም እኩል እድል የሚሰጥና ለሁሉም ግልጽ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓቱ አጠቃቀም ላይ ለንግዱ ማሕበረሰብ በሳምንት ሁለት ቀን ባለሥልጣኑ


አቶ ሀጂ ኢብሳ

በነጻ ሥልጠና እየሠጠ መሆኑን አውስተው፤ እስከ አሁን ለአራት ሺህ ሠልጣኞች ሥልጠና መስጠቱን ተናግረዋል፡፡

የንግዱ ማህበረሰብ የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓቱን ፈጥኖ በመረዳት እየተጠቀመበት መሆኑንም አክለው ገልጸዋል፡፡

በኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓቱ አቅራቢዎች ጨረታ ካሸነፉ በኋላ "ዋጋ ተወደደብኝ" በሚል እቃ ያለማቅረብ ችግር እንደሚያጋጥም የተናገሩት አቶ ሀጂ፤ ይህንን ለመቅረፍ የዕቃ ዋጋዎች የሚለዋወጡ በመሆኑ የጨረታው አሸናፊ እንደታወቀ መሥሪያ ቤቶች ሳያዘገዩ ግዢ መፈጸም እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

በተያዘው በጀት ዓመት በሲዳማ ክልልና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሙከራ ደረጃ ትግበራ እየተደረገበት መሆኑን ጠቁመው፤ በሂደትም በሁሉም ክልሎች የግዢ ሥርዓቱን ኤሌክትሮኒክስ በማድረግ የሀገርን ሀብት አላግባብ እንዳይባክን እንደሚደረግ አመላክተዋል፡፡

38ሺ የሚጠጉ የንግዱ ማህበረሰቦችም በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ግዢ እየፈጸሙ እንደሆነም በመድረኩ የተገለጸ ሲሆን በተያዘው በጀት ዓመት 15ሺ 360 ተጫራች ድርጅቶችም በኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት መመዝገባቸው ተጠቁሟል፡፡

የዓለም ባንክ ባጠናው ጥናት መሠረት በወረቀት ግዢ በአንድ ጨረታ አራት ተጫራቾች ይወዳደሩ እንደነበር አውስተው፤ አሁን በኤሌክትሮኒክስ ግዢ በአማካኝ ስምንት ተጫራቾች እየተሳተፉ መሆኑን ጥናቱ እንዳመላከተ ተነግሯል፡፡

ከዚህ በፊት በወረቀት በነበረው አሠራር መሥሪያ ቤቶች አንድ መገልገያ ዕቃ ለመግዛት በአማካኝ 216 ቀናት ይፈጅ እንደነበር የተገለጸ ሲሆን አሁን በተዘረጋው የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓት ዓለም አቀፍ ግዢዎችን ጨምሮ እስከ አንድ ወር ማጠናቀቅ እንደሚቻል ተጠቁሟል፡፡አሁን ላይ የጨረታ ሰነድ በኤሌክትሮኒክስ መንገድ በነጻ እየተሸጠ መሆኑም ተመላክቷል፡፡




# የዘውዲቱ ሆስፒታል ማስፋፊያ ግንባታ በአንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር እየተከናወነ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ማስፋፊያ ፕሮጀክት በአንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር እየተከናወነ እንደሚገኝ የትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት አስታወቀ፡፡ ማስፋፊያ ግንባታው 33 ነጥብ 3 በመቶ መድረሱ ተገልጿል፡፡

በትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ማስፋፊያ ፕሮጀክት ተወካይ አርክቴክት ነጋሽ መሐመድ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የዘውዲቱ ሆስፒታል ማስፋፊያ የሆስፒታሎችን ግንባታ ደረጃ ባሟላ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል።

የሆስፒታሉ የማስፋፊያ ፕሮጀክት በአንድ ሺህ ስምንት መቶ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ እየተከናወነ መሆኑን የገለጹት አርክቴክት ነጋሽ፤ ከአንድ ዓመት በፊት የተጀመረው የማስፋፊያ ግንባታው አፈጻጸም ከ33 ነጥብ ሶስት በመቶ በላይ መድረሱን አስታውቀዋል።

የግንባታው ሂደት አምስተኛ ወለል ላይ መድረሱን የገለጹት ተወካዩ፤ ግንባታው ስምንት ወለሎች የሚኖሩት በመሆኑ ቀሪ ሦስት ወለሎችን ሥራ በፍጥነት ለማጠናቀቅ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ የመጣውን የሕክምና ፈላጊዎች ቁጥር ታሳቢ በማድረግ ግንባታው መጀመሩን አንስተው፤ ማስፋፊያው ሲጠናቀቅ ሆስፒታሉ ተጨማሪ ከ200 በላይ የአልጋዎች ይኖሩታል ብለዋል።

ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የመድኃኒት መሸጫ፣ የህፃናትና የአዋቂዎች ሕክምና ክፍልች፣ የቀዶ ህክምና ፣የፊዚዮቴራፒንና አስቸኳይ ሕክምና መስጫ ክፍሎችና የተለያዩ አገልግሎት መስጫዎች እንደሚኖሩት አመላክተዋል።

በተጨማሪም በሆስፒታሉ የተሟላ የሕክምና አገልግሎት ለመስጠት የሚያችሉ የሠራተኞች ማረፊያና የአስተዳደር ክፍሎች እንደሚኖሩ ተናግረዋል፡፡

ፕሮጀክቱ የሆስፒታል ማስፋፊያ እንደመሆኑ መጠን ትልቅ የሜካኒካል ሥራዎች እንደሚጠይቅ ጠቁመው፤ የጤና ተቋማትን ደረጃ መሠረት በማድረግ የአየር ማስወገጃ፣ የንጽህና መጠበቂያ ሲስተሞችና ሌሎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች እንደሚገነቡ ተናግረዋል።

ቀደም ሲል የዘውዲቱ ሆስፒታል ከአቅሙ በላይ ታካሚዎችን ያስተናግድ እንደነበር ጠቅሰው፤ የማስፋፊያ ፕሮጀክቱ ታካሚዎች በተመቻቸ ሁኔታ የሕክምና አገልግሎት ማግኘት የሚገበትን ዕድል የሚፈጥር መሆኑን አስረድተዋል።

የዘውዲቱ ሆስፒታል በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ አንጋፋ ሆስፒታሎች መካከል አንዱ መሆኑን በመግለጽ ለታካሚዎች የተሻለ የህክምና አገልሎት መስጠት እንዲያስችል የማስፋፊያ ግንባታው እንደሚፋጠን ጠቁመዋል።

ባለፈው ዓመት የተጀመረው የሆስፒታሉ ማስፋፊያ ግንባታ በአንድ ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ቀነ ገደብ እንደተያዘለት አስረድተዋል።

የማስፋፊያ ፕሮጀክቱን በታቀደለት ጊዜ ለማጠናቀቅ ግንባታው እየተፋጠነ ይገኛል ያሉት አርክቴክት ነጋሽ፤ ለግንባታ የሚያስፈልግ የሲሚንቶ ግብዓት እጥረት ተግዳሮት በመሆኑ ችግሩን ለመቅረፍ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

# ‹‹ቻይና ከኢትዮጵያ ጋር በቱሪዝም ዘርፍ ይበልጥ ለመሥራት ቁርጠኛ ናት››

**- ሚስተር ሺን ኪንሚን**
**በኢትዮጵያ የቻይና ኤምባሲ ምክትል ኃላፊ**

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ቻይና ከኢትዮጵያ ጋር በቱሪዝም ዘርፍ ይበልጥ ለመሥራት ቁርጠኛ ናት ሲሉ በኢትዮጵያ የቻይና ኤምባሲ ምክትል ኃላፊ ሚስተር ሺን ኪንሚን ገለጹ፡፡ ሚስተር ሺን ኪንሚን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ቻይና በቱሪዝም ዘርፍ እስካሁን ካከናወነቻቸው የትብብር ሥራዎች በላቀ ሁኔታ በጋራ ለመሥራት ዝግጁ ናት።

ቻይናና ኢትዮጵያ በዘርፉ ውጤታማ ሥራዎች ለማከናወን እርስ በእርሳቸው የሚማሩበት ዕድል አላቸው ያሉት ሚስተር ሺን፤ የቻይና የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ኢትዮጵያን ከ30 ሀገራት መካከል አዲስ መዳረሻ አድርጎ መሰየሙ በዘርፉ በጋራ ለመሥራት ያለውን ፍላጎት ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

በቱሪዝም ዘርፉ ቻይና ኢትዮጵያን ተመራጭ ማድረጓ በርካታ ቻይናውያን ቱሪስቶች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ያበረታታል ሲሉ አስረድተዋል። አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን የአፍሪካ መዲናና የቻይና መግቢያ በር ናት ያሉት ሚስተር ሺን ፤ በከተማዋ ያለውን የኢኮ-ቱሪዝም ሥፍራዎች ማስፋፋት ለዘርፉ ዕድገት ወሳኝ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ትብብሩን ውጤታማ ለማድረግ ቀድሞ ለኢንቨስትመንት ምቹ የሆነ አካባቢ መፍጠር ያስፈልጋል ያሉት ሚስተር ሺን፤ የቤልት ኤንድ ሮድ ኢኒሼቲቭ በኢትዮጵያ የቱሪዝም ኢንዱስትሪው ለማሳደግ እንደሚረዳ ተናግረዋል፡፡

እንደ ሚስተር ሺን ገለጻ፤ ከሶስት ሺህ ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ጥንታዊ ሥልጣኔ ያላቸው ሁለቱ ሀገራት በቱሪዝም ዘርፉ ያላቸው እምቅ ሀብት በትብብር ቢያለሙ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ይችላሉ። ቻይናና ኢትዮጵያ የጀመሩት ሁሉን አቀፍ ስትራቴጂካዊ አጋርነት በተለይ የፖለቲካ ቅርርብ በኢኮኖሚውና በቱሪዝም ዘርፍ የበለጠ እንዲሠሩ የሚያስችል እንደሆነም ሚስተር ሺን ተናግረዋል።

የኢትዮጵያና የቻይና የሁለትዮሽ ግንኙነት በባህልና በታሪክ የተሳሰረ በመሆኑ ሁለቱ ሀገራት በቱሪዝም ኢንዱስትሪው ላይ ለውጥ ለማምጣት ሰፋፊ አማራጮች እንዳሏቸው ጠቁመዋል። ኢትዮጵያ የአፍሪካ መዲና በመሆኗ እንዲሁም ካላት ዕምቅ የቱሪዝም ሀብት አንጻር በዘርፉ በአጭር ጊዜ ለማሳደግ ሰፊ ዕድል እንዳላት ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ከጥንት ሥልጣኔዋ እንዲሁም ካላት ባህላዊና ታሪካዊ ቅርሶች የተነሳ ትልቅ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ አቅም አላት፤ ይህንን በመገንዘብ በትብብር በመሥራት የጋራ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

# የወተት ምርትን ለማሳደግ የሚረዳ የዝርያ ማሻሻያ መመሪያ ተግባራዊ ሊደረግ ነው

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- የወተት ምርትን ለማሳደግ የሚረዳ ሀገር አቀፍ የወተት ላም ዝርያ ማሻሻያ መመሪያ ተግባራዊ ሊደረግ መሆኑን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በሚኒስቴሩ የእንስሳትና ዓሣ መሪ ሥራ አስፈጻሚና የወተት ሀብት ልማት ዴስክ ኃላፊ አቶ ለማ ገመዳ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የወተት ምርትን ለማሳደግ የሚረዳ ወጥ የሆነ ሀገር አቀፍ የወተት ላም ዝርያ ማሻሻያ መመሪያ ተዘጋጅቷል።

የወተት ምርት ላይ ያተኮረ የሥነ-ተዋልዶ ባዮቴክኖሎጂ ዘዴዎች አተገባበር የሚል መመሪያ በማዘጋጀት ለተለያዩ ክልሎች መላኩን አመላክተዋል።

መመሪያውን ለማዘጋጀት አንድ ዓመት ያክል ጊዜ የወሰደ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ለማ፤ መመሪያው ከክልል እስከ ወረዳ ተግባራዊ እንዲሆን ለ300 ባለሙያዎች ሥልጠና ተሰጥቷል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ለማ ገለጻ፤ ከዚህ ቀደም በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የወተት ላም ዝርያ ማሻሻያ መመሪያ ባለመኖሩ የወተት ምርትን በሚፈለገው መጠን ማሳደግ አልተቻለም፡፡

አሁን የተዘጋጀው መመሪያ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉትን ላሞችን ዝርያ በማሻሻል የወተት ምርትን ለማሳደግ ይረዳል ብለዋል፡፡

ጥራቱን የጠበቀ የወተት ምርት እንዲኖር ከዝርያ ማሻሻል በተጨማሪ የመኖ አቅርቦትን ማሻሻል ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑን አቶ ለማ አስረድተዋል፡፡

81 በመቶ ኢትዮጵያ የወተት ምርት የሚገኘው ከዳልጋ ከብቶች ቢሆንም አብዛኛው እንስሳት የሀገር ውስጥ ዝርያ በመሆናቸው ዝርያቸውን ማሻሻል እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

የተሻሻሉ የወተት ላሞችን ቁጥር በሚፈለገው መጠን ለማሳደግ ትክክለኛ ዝርያና ምቹ የርባታ አካባቢን መምረጥ፣ የመኖ ዝግጅትና የእንስሳት እንክብካቤ ቁልፍ ጉዳይ መሆናቸውን አቶ ለማ አመላክተዋል።

በተጨማሪ የእንስሳት ጤና ምርመራ ሥርዓት አለመዘርጋቱ እንዲሁም ለዝርያ ማሻሻያ የሚሆኑ የሀገር ውስጥ ዝርያዎችን በተገቢው መልኩ አለመምረጥ ለሚፈለገው ውጤት አለመገኘት ተጠቃሽ ችግሮች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

አቶ ለማ አክለውም፤ መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ በዘርፉ የተሰማሩ አርብቶ አደሮችና ባለሙያዎችን ዕውቀትና ክህሎት ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

የወተት ሀብት ምርታማነትን በመጨመር የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እንዲሁም ኢትዮጵያ ከዘርፉ የምታገኘውን ገቢ ማሳደግ ያስፈልጋል፤ በዚህ ረገድ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ሚና መወጣት ይኖርባቸዋል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# አይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ኃይል ማመንጫ የሀገሪቷን የኃይል አቅርቦቱን ከማሳደጉ በተጨማሪ ለክልሉ ኢንቨስትመንት መስፋፋት የበኩሉን ሚና እንደሚጫወትም አስረድተዋል።

የፕሮጀክቱ መጠናቀቅ ከጂቡቲ አዲስ አበባ ለተዘረጋው የባቡር ትራንስፖርትና ለደረቅ ወደብ አገልግሎት ከፍተኛ ጥቅም እንደሚሰጥ ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለጂቡቲ የኤሌክትሪክ ኃይል በሽያጭ እያቀረበች መሆኑን የጠቆሙት አቶ ሞገስ ፤ ለሱማሌ ላንድና ሶማሌ ፕሮጀክቱ ተጨማሪ አቅም እንደሚፈጥርና ቀጣናዊ ትስስሩን እንደሚያቀላጥፍ ገልጸዋል፡፡

የአይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ኃይል በማመንጨት የሥራ ሂደትና በአጠቃቀም ምክንያት የሚፈጠር የኃይል መዋዠቅን ማረጋጋት የሚያስችሉ ዘመናዊ መሣሪያዎች ተገጥመውለታል ብለዋል፡፡

በቀጣይ በሶማሌ ክልል ብቻ አይሻ -3፣ አዲጋላ፣ ቱሉ ጉሌድ፣ ቀብሪ በያህ፣ የመሳሰሉ የንፋስ ኃይል ማመንጫዎችን የመገንባት እቅድ መኖሩን አስታውቀዋል፡፡

ፕሮጀክቱን በ18 ወራት ውስጥ ለማጠናቀቅ ዕቅድ ተይዞ እንደነበር አቶ ሞገስ አስታውሰው፤ ከፋይናንስ ጋር የተያያዙ መጓተቶች ለሥራው መፋጠን እንቅፋት መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ፕሮጀክቱ በ2011 ዓ.ም መጨረሻ ይጠናቀቃል ተብሎ ዕቅድ ተይዞለት ነበር። አበዳሪው ኤግዚም ባንክ በስምምነቱ መሠረት ገንዘብ በወቅቱ አለመልቀቁ በሥራው ሂደት ችግር መፍጠሩን የተናገሩት አቶ ሞገስ፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ለፕሮጀክቱ የሚወጣውን የተወሰነ የገንዘብ መጠን መክፈል ስለቻለ የፕሮጀክቱን ግንባታ ማስቀጠል እንደተቻለ አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ ከነፋስ ኃይል አንድ ነጥብ ሶስት ጊጋ ዋት ኤሌክትሪክ ማመንጨት የሚያስችል አቅም አላት።

# አውደርዕዩ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አቶ ስለሺ፤ የዘርፉ ተዋናዮች በአንድ ጣሪያ ስር በማገናኘት አገልግሎታቸውን እንዲያስተዋውቁና ለተሻለ ሥራ እንዲቀናጁ ማድረግ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀው ሀገር አቀፍ የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ዓውደርዕይ 154 ሺህ 799 የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች መጎብኘታቸውን አስታውቀዋል።

በተጨማሪም በአዲስ አበባ የሚኖሩ ከሶስት ሺህ በላይ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ አባላት አውደርዕዩን ጎብኝተዋል ያሉት አቶ ስለሺ፤ በተለያዩ የዲጅታል አማራጮች ደግሞ ከዘጠኝ ሚሊዮን ጊዜ በላይ መጎብኘቱን ገልጸዋል።

ዓውደ ርዕዩ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ከአንድ መቶ ጊዜ በላይ የዜና ሽፋን ማግኘቱን ጠቁመው፤ ይህም ሀገሪቷ ያላትን የቱሪዝም ሀብት በሰፊው ለማስተዋወቅ ዕድል የፈጠረ መሆኑን አስረድተዋል።

በዓውደ ርዕዩ የተገኘው ውጤት በቀጣይ ሰፊ ጊዜ ወስዶ ቢሰራበት የተሻለ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ትምህርት የተወሰደበት እንደሆነ አቶ ስለሺ አመላክተዋል።

ዓውደ ርዕዩ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ነው ያሉት አቶ ስለሺ፤ በቀጣይ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የቱሪዝም አውደ ርዕይ እንደሚዘጋጅ ተናግረዋል፡፡

በዓውደ ርዕዩ መዝጊያ ላይ ለኢትዮጵያ ቱሪዝም ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረከቱት አቶ ሃብተሥላሴ ታፈሰን የሚዘክር መጽሐፍ ተመርቋል፡፡

ለሀገር አቀፍ የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ አውደርዕዩ መሳካት አስተዋጽኦ ላበረከቱ አካላት የዕውቅናና ሽልማት መርሃ-ግብር ተከናውኗል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መስከረም 29 ቀን 2016 ዓ.ም ሀገር አቀፍ የቱሪዝም ሆስፒታሊቲ አውደርዕዩን መርቀው መክፈታቸው የሚታወስ ነው።

# የነዳጅ ድጎማ ያለአግባብ በተጠቀሙ

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እንደተናገሩት፤ ሚኒስቴሩ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት ሳይሰጡ የተጠቀሙትን የነዳጅ ድጎማ ተመላሽ የሚያደርጉበት አሠራር አለው። በዚህ መነሻ መሠረት በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት አገልግሎት ሳይሰጡ የነዳጅ ድጎማውን ያለአግባብ የተጠቀሙ ሁለት ሺህ 102 አሽከርካሪዎች ከአራት ሚሊዮን 416 ሺህ 143 ብር እንዲመልሱ ተደርጓል፡፡

በአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ በኩል እስከ ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም በተደረገ ቁጥጥር ከአንድ ሺህ 318 ተሽከርካሪዎች ሁለት ሚሊዮን 767 ሺህ በላይ ብር ተመላሽ እንዲያደርጉ ተደርጓል ያሉት አቶ ሰልማን፤ ተሽከርካሪዎቹ ተመላሽ ያደረጉት አገልግሎት ሳይሰጡ የተጠቀሙትን የነዳጅ ድጎማ ገንዘብ መሆኑን ገልጸዋል።

ከዚህ ቀደም በነበረው ሂደትም ተሽከርካሪዎች ከሐምሌ 2014 እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት ሳይሰጡ የተጠቀሙት የነዳጅ ድጎማ ብር 7 ሚሊዮን 183 ሺህ 381 እንደመለሱም ተናግረዋል።

በሩብ ዓመቱ ከድጎማ እንዲታገዱ የተደረጉ ተሽከርካሪዎች ከአምሥት ሺህ በላይ መድረሳቸውን የጠቆሙት ኃላፊው፤ በተመሳሳይ ከሐምሌ 2014 እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም ከነዳጅ ድጎማ ተጠቃሚነት የታገዱ ተሽከርካሪዎች ቁጥር 35 ሺህ መድረሳቸውን ገልጸዋል።

እንደ አቶ ሰልማን ገለፃ፤ የነዳጅ ድጎማ ሥርዓት ከተጀመረ አንስቶ እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ከ23 ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ ለተሽከርካሪዎች ድጎማ ተደርጓል። በ2016 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከስድስት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር በላይ ለተሽከርካሪዎች ድጎማ ተደርጓል።

በድጎማ ሥርዓቱ የሚካተቱ ተሽከርካሪዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ 240 ሺህ 890 ተሽከርካሪዎች ወደ ዲጂታል ሥርዓቱ ገብተዋል ያሉት አቶ ሰልማን፤ በሩብ ዓመቱ ዘጠኝ ሺህ 872 ተሽከርካሪዎች ለድጎማ ተመዝግበዋል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የፕሪቶሪያውን ስምምነት ሙሉ በሙሉ ስመተግበር መንግሥት የወሰደው ቁርጠኛ ርምጃ የሚበረታታ ነው!

በሰሜን ኢትዮጵያ ለሁለት ዓመታት ያህል የዘለቀውና የብዙዎችን ሕይወት የቀጨው፤ ያፈናቀለውና ለስደት የዳረገው ጦርነት የተቋጨበት የፕሪቶሪያው ስምምነት ከተፈረመና ኢትዮጵያም ፊቷን ወደ ሰላም ካዞረች አንድ ዓመት ተቆጠረ፡፡

በዚህ አንድ ዓመት ሰላም ከመስፈኑ ባሻገር የትግራይ፤ የአማራና የአፋር አርሶ አደሮች ወደ ግብርና ሥራቸው ተመልሰዋል፤ የወደሙ መሠረተ ልማቶችን እንደገና የማቋቋም ሥራዎች ተጀምረዋል፤ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ተመልሰዋል፤ የተፈናቀሉ ዜጎችም ወደ ቀያቸው ተመልሰው ሰፍረዋል፡፡ በአጠቃላይ ሕይወት ከጦርነቱ በፊት እንደነበረችው ለመመለስ በመንግሥትና በሌሎች ግብረ ሰናይ ድርጅቶች እንዲሁም በመላው ሕዝብ ተሳትፎ የተለያዩ ተግባራት ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡

በተለይም መንግሥት በጦርነቱ በእጅጉ የተጎዳውን የትግራይ ሕዝብ መልሶ ለማቋቋምና ጦርነቱ ያሳረፈበትን ሥነልቦና ለማከም በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ ከስምምነቱ መፈረም በኋላ የጥላቻውን ጉም በመግፈፍ ወደ ትግራይ በግንባር ቀደምነት የተጓዘው በአፈ ጉባዔው የተመራው የፌዴራል መንግሥቱ ልዑክ ነበር። ይህ ልዑክ ከተጓዘ በኋላ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የባንክና የአውሮፕላን አልግሎቶች በፍጥነት እንዲጀምሩ ተደርገዋል።

የትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር በተመሠረተ ጊዜ መሳሳብና መጓተትን ለማስቀረት ሲባል የአመራሩን ድርሻ ክልሉ እንዲወስድ በማድረግ ጊዜያዊ አስተዳደሩ ፋታ አግኝቶ ፊቱን ወደ ሰላምና ልማት እንዲያዞር ተደርጓል።

የግብርና ሥራውን ለማገዝ የሚመለከተው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በክልል ደረጃ ከሚጠበቅበት በላይ ሠርቷል። ዩኒቨርሲቲዎችንና ትምህርት ቤቶችን ወደ አገልግሎት ለመመለስ የትምህርት ሚኒስቴር በርካታ ተግባራትን አከናውኗል። በክልሉ ተቋርጦ የነበረውን ትምህርት እንዲጀመር ከማድረግ ባሻገር ከሁለት ዓመታት በኋላ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ተማሪዎች እንዲወስዱ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ተችሏል፡፡

የመከላከያ ሠራዊት የሕዝቡን ችግር ለመፍታት ከራሱ በጀት ቀንሶ አያሌ ተግባራት አከናውኗል። የሰላም ስምምነቱን እንደ ዕድል በመጠቀም ሕዝብን ከችግር በማዳን፣ መንግሥታዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን በማስመጀር ኃላፊነቱን ተወጥቷል። ከፌዴራል መንግሥቱም አልፎ ክልሎች ከአነስተኛ በጀታቸውና ገቢያቸው በመቀነስ የትግራይ ክልልን ደግፈዋል።

ሆኖም በመንግሥት በኩል የተደረገውን ያህል የሚመጥን ምላሽ ከዚያኛው ወገን አልተገኘም፡፡ በሰበብ አስባቡ የፕሪቶሪያውን ስምምነት የሚጋፉ ድርጊቶችና አሉታዊ ሃሳቦች ጭምር በየጊዜው ሲደመጡና ሲታዩ አንድ ዓመቱ አልፏል፡፡ የፕሪቶሪያው ስምምነት የሰላም ስምምነቱን የፈረሙ አካላት ከአሉታዊ ድርጊቶችና ንግግሮች እንዲታቀቡ የሚያስገድዳቸው ቢሆንም ሌላኛው ወገን አካላት ስምምነቱን የሚጥሱ ድርጊቶችና ሃሳቦችን ሲያንጸባርቅ ታይቷል፡፡

ሆኖም የፕሪቶሪያው ስምምነት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት የሚያጸናና የዜጎችን ሰቆቃ የሚቀርፍ ስምምነት በመሆኑ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሚተገበር ነው፡፡ ስምምነቱ የኢትዮጵያን መሠረት ከማጽናቱም ባሻገር በጦርነት ሰቆቃ ውስጥ የነበሩትን የትግራይ፤ የአማራና የአፋር ሕዝቦችን እፎይታ ያጎናጸፈ ነው ፡፡

ከፕሪቶሪያው ስምምነት ቀጥሎ የተካሄደው የናይሮቢ ስምምነት መተማመንን የፈጠረና ኢትዮጵያ የጀመረችውን የሰላም መንገድ የሚያጸና ነው፡፡ በተለይም በጦርነቱ ምክንያት የተቋረጡ መሠረተ ልማቶችንና ሰብዓዊ ድጋፎችን በሚፈለገው መልኩ ለማድረስ መሠረት የጣለ ነው፡፡ በዚሁ መሠረትም በትግራይ፤ በአማራ እና በአፋር ክልሎች ተቋርጠው የነበሩ የቴሌኮሙኒኬሽን፤ የኤሌክትሪክና የባንክ አገልግሎቶች መልሰው ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ለማድረግ አስችሏል፡፡

ስለዚህም ለሀገር ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነትን መሠረት ያደረገውና የዜጎች ሰቆቃ እንዲያበቃ ያደረገው የፕሪቶሪያው ስምምነት መፈጸም ከሁሉም ወገን የሚጠበቅ ግዴታ ነው፡፡ ያለውም ብቸኛ አማራጭ ይህንን ስምምነት መፈጸምና ማስፈፀም ብቻ ነው።

ነገር ግን ከመንግሥት ውጪ ያሉ አካላት እነዚህን ስምምነቶች በተደጋጋሚ ሲጥሱ ይታያሉ፡፡ ይህ ደግሞ እንደ ሀገር የሰፈነውን የሰላም አየር የሚበርዝና ዳግም ወደ ጥፋት የሚወስድ በመሆኑ ሊታረም ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በርግጥም የሰብአዊ ድጋፍን በራስ አቅም መሸፈን የሉአላዊነትና የክብር ጉዳይ ነው

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት ያለፈችባቸው የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች የበርካታ ችግሮቿ ጠባሳዎች ናቸው። ይህ እውነታ ለሰብአዊ እርዳታዎች እጇቿን ወደሌሎች ሀገራት እንድትዘረጋ ሲያስገዳዳት ቆይቷል።

ሀገራችን እስከዛሬ በውስጥና በውጭ ኃይሎች በተነሱባት ጦርነቶች የሕይወት ጥፋትና የንብረት ወድመት ሰለባ ሆናለች። ይህን ተከትሎ በሚፈጠሩ ስደትና መፈናቀሎችም በርካታ ሰብአዊ ጉዳቶች አጋጥመዋታል። የጦርነት ክፋት መልከ ብዙ ነው። በሰው ልጆች ላይ ከሚያደርሰው መቅሰፍት ባለፈ የሚያስከትላቸው ችግሮች ተዘርዝረው አያልቁም።

ጦርነት ባለበት ሀገር ገበሬው ከአርሻው አይውልም። ከአውድማው እህል ከቡቃያው ምርት አይታይም። ሰኔ ሐምሌ፣ እሸት፣ ልምላሜ ይሏቸው በረከቶች ሁሉ የ‹‹ነበር›› ታሪክ ይሆናሉ። ጦርነት ሀገር ይፈታል፣ ቤተሰብ ይበትናል። ከመንደር ቀዬ አፈናቅሎ ባሕር አሻግሮ ያሰድዳል። ጦርነት ያየው ሕዝብ ከመንደሩ ውሎ አያድርም። ነፍሱን ለማዳን ቤት ንረቱን ጥሎ ይፈናቀላል።

ለእንዲህ ዓይነት እውነታዎች አዲስ ያልሆነው የሀገራችን ሕዝብ በስደትና መፈናቀል መንገዶች ደጋግሞ ተመላልሷል። እንዲህ በሆነ ጊዜ ከውጭ ሀገራትና ከራስ ወገን ጓዳ ‹‹እነሆ›› የሚሉ እጆች መጣመራቸው ሰብአዊ ድጋፎች መበርከታቸው ዕሙን ነው ።

ከራሷ ዜጎች ባለፈ በጦርነት ሳቢያ የሚሰደዱ የውጭ ሀገራት ዜጎችን ተቀብላ ማስተናገዷም አዲስ አይደለም። አሁንም ድረስ ይህቺን ምድር በእንግድነት የሚረግጡ ስደተኞች የዓመታት ኑሮን እያሳለፉ ይገኛሉ። ይህ እውነታ እንዳለ ሆኖ በሀገራችን ሕዝቦች ላይ አሁንም ድረስ የሚደርሰው መፈናቀል የትኩረት ዓይኖች እንዲያርፉበት የሚያሻው ነው።

በጦርነትና ድርቅ ምክንያት ከመኖሪያ ቀያቸው የሚፈናቀሉ ወገኖች ምንጊዜም የሌሎች አካላት እገዛና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። ይህ ዓይነቱ ችግር እየተደጋገመ ሲመጣ ደግሞ ሁሌም እጅን ለእርዳታ ከመዘርጋት የሚያሳጥር መላና መፍትሔ መቀየሱ አይቀሬ ይሆናል።

ከሰሞኑ ይፋ የሆነውና ይህን ሀቅ የሚያረጋግጠው የመንግሥት ሃሳብ በጉዳዩ ላይ ትኩረት እንዲሰጥበት አመላካች የመሆን ፋይዳ አለው። በኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን በኩል የተሰጠው መግለጫ እንደሚያመላክተው፣ የሰብአዊ ድጋፍን በራስ አቅም መሸፈን የሉአላዊነትና የክብር ጉዳይ ጭምር ነው።

የብሔራዊ አደጋ ስጋት አመራር ምክር ቤት ሰብሳቢው አቶ ደመቀ እንዳሉት፣ ኢትዮጵያ በራሷ አቅም ለራሷ ምላሽ መስጠት መቻሏ ሰብአዊ ድጋፍ ለሚያሻቸው ወገኖች አቅምን ይፈጥራል። ይህ ተግባራዊ ይሆን ዘንድም የተቀናጀ ርብርብ ማድረግ ይጠበቃል።

በዓመታዊው የብሔራዊ አደጋ ስጋት አመራር ምክርቤት መደበኛ ስብሰባ ላይ እንደተጠቆመው የልማት ሥራዎችን ማጠናከር የሰብአዊ ድጋፉን በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማጎልበትና አቅምን ለመገንባት ያግዛል።

በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን የተለያዩ ስፍራዎች የተፈናቃይ ወገኖች ቁጥር በብዛት ተመዝግቧል። ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉትም በክልሎች ለሚገኙና አፋጣኝ ምላሽ ለሚያሻቸው ተፈናቃዮች ዝርዝር ዕቅድ ማዘጋጀት ተገቢነት ይኖረዋል።

እስካሁን በነበሩ ተሞክሮዎች በየጊዜው ለሚያጋጥሙ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች እርዳታ የመጠየቅ ልማድ አዲስ ሆኖ አያውቅም። አሁን ግን ችግሩን በዘላቂነት ለመቋቋም የሚያስችል ጠንካራ ራስን የመቻል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ራስን ከተረጂነት አላቆ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ ለመድረስም በጋራ የመሥራት አስፈላጊነትን አቶ ደመቀ አስምረውበታል። ለዚህም ክልሎች በአካባቢያቸው ችግሮች እንዳይከሰቱ ከማድረግ ባለፈ በራሳቸው አቅም ተገቢውን ምላሽ የመስጠት አቅምን ሊያዳብሩ ይገባል።

ኢትዮጵያ ላለፉት በርካታ ዓመታት ባጋጠሟት ችግሮች ከተረጂነት ልማድ ሳትወጣ ቆይታለች። ይህ እውነታም ለራሷ ችግር ራሷ እንዳትደርስ ምክንያት ሆኖ ነበር። በስብሰባው ላይ እንደተጠቀሰውም ይህ ዓይነቱ ሀቅ ሀገራችን በሉአላዊነቷ ምሉዕ ሆና እንዳትዘልቅ አድርጓታል።

የብሔራዊ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ዶክተር ሽፈራው ተክለማርያም በበኩላቸው እንደገለጹት ፣ የሀገርን ክብር አስጠብቆ ከተረጂነት ለመላቀቅ የሰብአዊ ድጋፍ ፍላጎትን በራስ አቅም መሸፈን ሊለመድ ይገባል።

ተደጋግሞ እንደሚነገረው ከተፈናቃዮች እርዳታ ጋር ተያይዞ ሊፈጸሙ የሚችሉ የሙስና ተግባራት የአገልግሎቱ ስጋት ናቸው። የስብሰባው ሃሳብ እንደሚጠቁምው ግን ለእንደህ ዓይነቱ ችግር ትክክለኛውን የተረጂዎች ቁጥር አስቀድሞ መለየት አንዱ መፍትሔ ይሆናል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ እርዳታን ላልተገባ ጥቅም የሚያውሉ ራስ ወዳዶችን በሕግ ተጠያቂ ማድረግ የግድ ይላል። ጠንካራ የሚባል ተቋማዊ አደረጃጀትን በማስፋትም ከተረጂነት ስሜት መላቀቅ አስፈላጊ ነው።

በሀገራችን በተለይ በድርቅ ምክንያት የሚፈናቀሉ ወገኖች በሚያጋጥማቸው የከፋ ችግር ከቀያቸው ርቀው ይጓዛሉ። ለዚህ መሰሉ ችግር መፍትሔ ለመሻትም በኢትዮጵያ የተለያዩ ስፍራዎች የሚገኙ ቦታዎችን ማልማት ተገቢ ይሆናል።

በስብሰባው እንደተጠቀሰው ደግሞ፣ በሀገሪቱ የተሟላ የመስኖ ልማት ከተዘረጋለት 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ እስካሁን መልማት የቻለው 65 በመቶው ብቻ ነው። በመሆኑም ቀሪውን ቦታ በመንግሥት ደረጃ በማልማት የታሰበውን ዓላማ ዕውን ማድረግ ይቻላል።

የታሰበውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ክልሎች የሚያዝላቸውን በጀት በተገቢው መንገድ ሊጠቀሙበት ይገባል። የገንዘብ ሚኒስትሩ አሕመድ ሽዴ እንዳሉትም፣ ክልሎች በየጊዜው የሚመደብላቸውን የእርዳታ በጀት በአግባቡ ማስተዳደር ኃላፊነታቸው ሊሆን ይገባል።

ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የሚገኘውን በረከት ዕውን ለማድረግ ምርቱ በተገቢው መንገድ ለተጠቃሚው ሊደርስ ይገባል። ለዚህ ደግሞ የገበያው ሥርዓት በአግባቡ ተመርቶ ለኅብረተሰቡ ተደራሽ መሆን አለበት። በገበያው ላይ የሚስተዋሉ ስብራቶችን ጠግኖ ክፍተቶችን ለመሙላትም የሚመለከታቸው አካላት ተሳትፎ አስፈላጊ ነው። ለዚህ ተግባራዊነትም ከፌዴራል እስከ ወረዳ የሚዘረጉ መዋቅሮች በአግባቡ ኃላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል።

የሰው ሠራሽና ተፈጥሮ አደጋዎች ሲደርሱ ለሀገር ከፍ ያለ ድህነት ያቀብላሉ። ሕዝቦች በተገቢው መንገድ በዕድገት ጎዳና እንዳይራመዱም ጋሬጣና ዕንቅፋቶች ናቸው። በነዚህ ችግሮች መዘዝ ሀገር ኢኮኖሚዋ ይሳሳል። ጓዳዋ ይራቆታል። ህልውናዋ ከአደጋ ስለሚወድቅም በሌሎች ሀገራት ደጋፊነት እንድትቀጥል ትገደዳለች።

ለዜጎች መፈናቀል ምክንያት የሚሆኑ ችግሮችን ከማጥናትና አስቀድሞ መፍትሔ ከመስጠት ባለፈ ችግሩ ሲከሰት የራስን መላ ማፈላለግ ተገቢ እንደሚሆን ይታመናል። ለዚህም ከመንግሥት ለውጡ በኋላ ተግባራዊ መደረግ የጀመሩትን የሌማት ቱርፋት፣ የበጋ መስኖና መሰል እንቅስቃሴዎች ወደተግባር መለወጥ ያስፈልጋል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን እንዳሉትም! የሰብአዊ ድጋፍን በራስ አቅም መሸፈን የሉአላዊነትና የክብር ጉዳይ ነው። የሀገርን ክብር በማስጠበቅ ከተረጂነት ለመላቀቅም የሰብአዊ ድጋፍ ፍላጎትን በራስ አቅም መወጣትን መላመድ ይገባል።

ሰብአዊ ድጋፍን በራስ አቅም መወጣት ብሔራዊ አርበኝነትን የሚጠይቅ የቁርጠኝነት ስሜት ነው። ኢትዮጵያ በሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ለተጎዱ ወገኖቿ በራሷ አቅም ተግባራዊ ምላሽ እንድትሰጥም የሁሉም አካላት ሀብረት ክንደ ብርቱ ሊሆን ግድ ይለዋል።

እንዲህ ሲሆን ሰው የመሆን ትርጉሙ ይደምቃል። ሰብአዊነት ቃሉ ይገዝፋል። ኢትዮጵያዊነት ይሉት ስም ከቦታው ይገኛል። አንድነትና መተሳሰብ ዕውን ሆኖም ‹‹ከራስ ቆርሶ ለራስ ማጉረስ›› ብሂል በተግባር ይታያል።

# የጋራ መኖሪያ ቤት በማስተላለፍ ሂደት ላይ የመምህራን ቅሬታ

ሞገስ ተስፋ እና ክፍለዮሐንስ አንበርብር

**ጉዳዩ፤**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ2009 ዓ.ም የጋራ መኖሪያ ቤት በኪራይ መልኩ የተቀበሉ መምህራን በ1997 ዓ.ም የጋራ መኖሪያ ቤት ተመዝግበው ሲቆጥቡ የቆዩ በ13 ኛው ዙር የዕጣ ዕድለኛ የሆኑት በዕጣ በወጣላቸው እና በኪራይ እየኖሩበት ያለው ቤት ተመሳሳይ ከሆነ በአንዱ ውል እንዲይዙ ምርጫ ተሰጣቸው፡፡መምህራኑም በምርጫቸው መሠረት በኪራይ መልኩ ይዘውት የነበረውን ቤት መረጡ፤ ውል ለመዋዋልም ተንቀሳቀሱ።

በወቅቱም መዋዋል የምትችሉት በ13ኛው ዕጣ ዋጋ ነው ተባሉ። ይህም ትልቅ ቅሬታና አለመግባባት ፈጠረ። በ2011 ዓ.ም የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በተመለከተ የወጣውን መመሪያ የሚጥስ እንደሆነም መምህራኑ አመለከቱ፡ ፡በመመሪያው መሠረት መስተናገድ አልቻልንም ሲሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የመልካም አስተዳደርና ምርመራ ቡድን ቅሬታቸው አቀረቡ፡፡

## የመምህራን ቅሬታ፤

በ2009 ዓ.ም የቤት ኪራይ ከተላለፈላቸው 5000 መምህራን መካከል የተወሰኑት 1997 ዓ.ም የጋራ መኖሪያ ቤቶች ተመዝጋቢ በመሆናቸው ቤት ደርሷቸዋል፡፡ ይህንንም ተከትሎ በ2011 ዓ.ም ለመምህራን በኪራይ ስለሚቀርቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለማስተላለፍና ለማስተዳደር በወጣው መመሪያ ቁጥር 01/2011 መሠረት፤ በኪራይ መልኩ እየኖሩበት ያለውና በ13ኛው ዙር ዕጣ የደረሳቸው ቤት ተመሳሳይ ከሆነ በኪራይ በያዝነው ቤት ውል መዋዋል እንደምንችል የሚገልጽ ነው፡፡

ይህንን የቤቶቹን የወቅቱን ዋጋ ተገማች ያደረገ መመሪያ መሠረት በማድረግ፤ በዕጣ የደረሰን ቤትና በኪራይ መልኩ እየኖርንበት ያለው የጋራ መኖሪያ ቤት ተመሳሳይ ስለሆነ መቀየር እንፈልጋለን ብለን አመለከትን፡፡ መመሪያውን ታሳቢ ባደረገ መልኩም መቀየር ትችላላችሁ የሚል ምላሽ ተሰጠን ይላሉ፡፡

መመሪያው በሚለው መሠረት ሂደቱን ተከትለን ለማስፈጸም መንቀሳቀስ ጀመርን፡፡ይህ ሲሆን የአዲስ አበባ ቤቶች ኤጀንሲ የአሁኑ የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን እስካሁን ድረስ ስንከፍል የነበረው የቤት ኪራይ ሳይያዝ፤ ቤቱ በወቅቱ በነበረው ዋጋ ማስተላለፍ ሲገባቸው በ13ኛው ዙር ዕጣ በወጣበት በ2013 ዓ.ም በኮዬ ፈጬ ዋጋ እንዲተላለፍ አደረጉ፡፡

እኛም አሠራሩ ትክክል አይደለም፤ ልንስተናገድ የሚገባው /በ2009 ዓ.ም ባለው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዋጋ ነው በሚል ቅሬታችንን ይዘንን እንዲያስተናግዱን አቤት አልን። የቤቶች ልማት ምላሽ ግን እኛ ትክክል ነን፤ በመመሪያው መሠረት ነው የሠራነው የሚል ሆነ፡፡

በዚህ ሂደት ላይ የአዲስ አበባ ካቢኔ ጥያቄያችን በሚቀበልና ትክክለኛነቱን በሚያረጋግጥ መልኩ ውሳኔ አሳለፈ፡፡ይህን መሠረት በማድረግም ጥያቄያችንን ብናቀርብም በአግባቡ አዳምጦ ለማስተናገድ ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡በወቅቱ የሚሰጡን ምላሽም ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ዕዳ አለበት፤ እናንተን አናስተናግድም አሉ፡፡

የምናስተናግዳችሁ የከተማ አስተዳደሩ ከመወሰኑ በፊት ባለው ነው ጨርሳችኋል የሚል ምላሽ እንደተሰጣቸው በመጠቆም፤ለጉዳያችም ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን አልቻሉም፤ ስለችግሩም የከተማው ትምህርት ቢሮ እና መምህራን ማኅበሩም ያውቃሉ፡፡

ካቢኔው የወሰነው ውሳኔ የእኛን ጥያቄ በሚደግፍ መልኩ በመሆኑ ልንስተናገድ የሚገባን ባቀረብነው ውሳኔ ነው የሚሉት መምህራኑ፤ የቤቱን ውል ልንዋዋል የሚገባን በ2009 ዓ.ም በነበረው ዋጋ እንጂ በ13ኛው ዙር ዕጣ በወጣበት ዋጋ አይደለም ባይ ናቸው፡፡በተጨማሪም እስካሁን በኪራይ መልክ ስንከፍለው የነበረው ገንዘብ እንደ ወጪ አልተያዘልንም የሚልም ቅሬታ አላቸው፡፡

ከመመሪያው ውጪ በ13ኛ ዙር ዕጣ ዋጋ እንድንስተናገድ የተፈለገው ለምንድን ነው? ፤ በ2009 / በ2013 ዓ.ም ባሉት የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዋጋ መካከል በአንድ ቤት ከ50ሺ ብር በላይ የዋጋ ልዩነት አለው፡፡ ይህን የዋጋ ልዩነት መክፈል ለእኛ ለመምህራን ከባድ ነው ሲሉም ቅሬታቸውን ያቀርባሉ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ
የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን
CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA
HOUSING DEVELOPMENT AND ADMINISTRATION BUREAU
HOUSING DEVELOPMENT CORPORATION

Date መጋቢት 2-9-2013 Ref.no /ቤ/ል/ኮ/ ቁ1/19/8938

ለአቤቱታ አቅራቢ መምህራን

አ/አበባ

ጉዳዩ፡- ለቀረበዉ ቅሬታ/አቤቱታ ከመመሪያ አንጻር መልስ መስጠትን ይመለከታል

በቀን 02/07/13 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ከአሁን በፊት ለመምህርን መንግስት ባመቻቸዉ ፕሮግራም በኪራይ ጋራ መኖሪያ ቤት አግኝታችሁ እየኖራችበ ት መሆኑን በምለጽ በጋራ መኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ተመዝግባችሁ ስትጠባበቁ በ13ኛዉ ዙር እጣ ባለ እድል መሆናችሁን በመግለጽ ለመምህራን በኪራይ ስለሚቀርቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለማስተላለፍና ለማስተዳደር በወጣዉ መመሪያ ቁጥር 1/2011 ክፍል 4 በአከራየና ተከራየ መብትና ግዴታ በተዘረዘረዉ ቁጥር 20 ልዩ የተከራይ መብት ንኡስ ቁጥር 3 ላይ በተገለጸዉ መሰረት፣ መምህሩ የቤት ኪራይ ተጠቃሚ ሆኖ መንግስት በዘረጋዉ የቤት ልማት ፕሮግራም በራሱ ወይም በትዳር አጋሩ ስም የቤት እጣ ከደረሰዉ ተመሳሳይ የቤት ዓይነት ከሆነና በኪራይ የያዙትን ቤት ከፈለጉ በወቅቱ በሚኖረዉ የጋራ መኖሪያ ቤት ማስተላለፊያ ዋጋ ግምት ተሰልቶ በረጂም ጊዜ ሽያጭ በስሙ እንዲተላለፍለት ይደረጋል ይላል ነገር ግን በ13ኛው ዙር ቤት ደርሶን ቅያሬ በመጠየቅ በመመሪያው መሰረት መዋዋል ሲገባን፡-

1. በ13ኛዉ ዙር የቤት ማስተላለፊያ ዋጋ እንድንዋዋል መደረጋችን መመሪያዉን የጣሰ በመሆኑ፣
2. በተለያዩ ዙሮች የተላለፉ ቤቶችን በአንድ አይነት የማስተላለፊያ ዋጋ እንድንከፈፍል መደረጋችን፣
3. ሙሉ እድሜውን በመምህርነት እስከጡረታ እያገለገለ ያለዉን መምህር ተጠቃሚነት ያላገናዘበ እና መመሪያ ተራ ቁጥር 20 ንኡስ ቁጥር አንድን ከግመምት ውስጥ ያላስገባ አሰራር እየተሰራ መሆኑ፣
4. ተመሳሳይ የቤት ዓይነት በተለዋጭ ተተክተዉ ለሌላ ለሚተላለፍለት ወገን የማስተላለፊያ ዋጋ እና እየኖርንበት ያለዉ ኮንዶምኒየም የተላለፈበት ዋጋ ከግምት ውስጥ ያለስገባ በመሆኑ የከተማ አስተዳደሩ ለመምህራን በኪራይ ስለሚቀርቡ መኖሪያ ቤቶች በወጣዉ መመረያ መሰረት እንዲያዋዉለንና እና በወቅቱ በሚኖረዉ የማስተላለፊያ ዋጋ እንድንከፍል ስንል በሙሉ ድምጽ በፊርማችን በማረጋገጥ እናመለክታለን በማለት በጠየቃችሁት መሰረት፡-

ሁሉም ጥያቆዎቻችሁ በአንድ ጉዳይ ላይ ማለትም በወቅታዊ የጋራ መኖሪያ ቤት ማስተላለፊመያ ዋጋ እንድንከፍል መደረጉ መመሪያ የጣሰ ስራ ተፈጽሞብናል የሚል እና የመምህራንን ተጠቃሚነት ያላገናዘበ አሰራር እየተሰራ ነው የሚል ነዉ፡፡ይሁንና ተቋሙ በመመሪያና አሰራር የሚመራ በዚህም መሰረት በ13ኛዉ ዙር የጋራ መኖሪያ ቤት እጣ እድለኞች ሆነዉ በኪራይ ከያዙት ቤት ጋር ተመሳሳይ ለሆነ መምህራን በእጣ የደረሰን ቤት ተመላሽ ተደርጎ በኪራይ የተሰጠን ቤት በመመበሪያዉ መሰረት በሽያጭ ይተላለፍልን ብላችሁ ባቀረባችሁት ጥያቄ መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ለመምህራን በኪራይ ስለሚቅርቡ ቤቶች ለማስተላለፍና ለማስተዳደር በወጣዉ መመሪያ ቁጥር 1/2011 ክፍል አራት፡-

-0118-33-35-53 ዜጉችን የቤት ባለቤት በማድረግ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እናረጋግጣለን 0118-12-23-65 E-Mail aahdpo@telecom.net.et
0118 12234 75

## የኮርፖሬሽኑ ምላሽ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የጋራ መኖሪያ ቤቶች ማስተላለፍ ዳይሬክተር ካሳሁን ዘውዴ በመምህራኑ ቅሬታ ዙሪያ ፤ በሰጡት ምላሽ፤ የጋራ መኖሪያ ቤቱ በ2009 ዓ.ም በኪራይ መልኩ ለመምህራን ተሰጥቷቸው ነበር፡፡ከዚያም ሐምሌ 3/2013 ዓ.ም ላይ በኪራይ የነበሩ ቤቶች በሙሉ /በወቅቱ በተላለፈበት ወቅቱ ሲባል/ 2009 ዓ.ም በተላለፈበት ዋጋ ግምት ውስጥ ገብቶ ለመምህራን እንዲሰጥ በካቢኔ ተወስኗል፡፡

መመሪያው በወቅቱ ሲል መምህራኑ ቤቱን ባገኙበት ወቅት በነበረው ዋጋ ማለቱ ነው፡፡መመሪያ በተለያየ መልኩ የኪራይ ቤቱን የያዙ ሲልም ከኪራይ ውጪ በዕጣ የደረሳቸው መምህራ አሉ ማለት ነው ፡፡ መምህራኑ የተሰጣቸው አንድ ዕድል ነው፡፡ከሁለቱ አንዱን ዕድል መምረጥ ይገባቸዋል፡፡ይህም የያዙትን ቤት ይዘው መቀጠል ወይም ደግሞ ዕጣ የወጣላቸውን ቤት መያዝ ነው፡፡

ስለዚህ በኪራይ ቤት ይዘውት የነበረውን ቤት ለመውሰድ ሲወስኑ፤ በዕጣ የወጣላቸው ቤት ላይ ቤቱ ለራሳቸው ስለወጣ፤ የወጣላቸውን ቤት ተመላሽ በማድረግ በኪራይ መልክ እየኖሩበት ያለውን መዋዋል ይችላሉ፡፡ልዩነት የሚፈጥረው የሚዋዋሉበት ዋጋ ነው፡፡

ዕጣ የወጣላቸው በ13ኛ ዙር ከሆነ ዕጣ በወጣላቸው ዋጋ /በወቅቱ ሲስተም ውስጥ በተቀመጠው ዋጋ / ገንዘቡን ከፍለው ይዋዋላሉ፡፡ በኪራይ የነበሩበትን ቤት ይዘው መቀጠል የሚፈልጉ ደግሞ በሁለት መልኩ ይስተናገዳሉ፡፡ አንደኛው ልክ ዕጣውን በሚዋዋሉበት ጊዜ የዕጣውን ልመልስና በኪራይ የያዝኩት ላይ አሁን ባለው በወቅቱ ዋጋ ልስተናገድ ማለት ነው፡፡ይህንን ሲወስኑ በወቅቱ ሲስተሙ ውስጥ በገባው ዋጋ ይስተናገዳሉ፤ በዚህም አግባብ የተስተናገዱ አሉ።

የከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ በጉዳዩ ላይ ሐምሌ 3 ቀን 2013 የደረሰበት ውሳኔ ፤ በኪራይ የነበሩ ቤቶች በወቅቱ በነበረው ዋጋ ማለትም በ2009 ዓ.ም በነበረው ዋጋ እንዲስተናገዱ የሚጠይቅ ነው፡፡ከሐምሌ 3 ቀን 2013 በኋላ የነበሩ ጥያቄዎችም በዚሁ አግባብ ተስተናግደዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ማብራሪያ ከሆነ፤ እስካሁን ያልከፈሉና ያልተስተናገዱ ካሉ ቢመጡ በ2009 በነበረው ዋጋ ይስተናገዳሉ፡፡ቀድመው የከፈሉትና ውል የያዙት ግን ብሩ ሊመለስላቸው አይችልም፡፡ምክንያቱም የገባው ወደ መንግሥት ካዝና ነው፡፡ውሳኔው ወደ ኋላ ጎትተንና መልሰን ሰዎችን ተጠቃሚ የምናደርግበት አግባብ የለም፡፡ ይህ ዕድል ነው፡፡

በዚህ መሠረት መስተናገድ የሚፈልጉ መምህራን ወደ ቤቶች ልማት መጥተው መስተናገድ ይችላሉ፤ እስካሁን ሲኖሩበት የነበረው የመንግሥት ቤት በእጃቸው መኖሩንና ኪራይ መክፈላቸውን የሚያሳይ መረጃና ከትምህርት ቢሮ የተጻፈ ደብዳቤ ይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡ቤቱ የተሰጠው ለመምህራን እና ለትምህርት ቢሮ ከመሆኑ አንጻር ፤ ትምህርት ቢሮ የሚያስፈልገውን መረጃ ትክክለኝነት አረጋግጦ መላክ እንደሚኖርበትም ኃላፊው አመልክተዋል፡፡

## ከሰነዶች የተገኙ መረጃዎች ለኮርፖሬሽኑ የተጻፈ ቅሬታ፤

መምህራን ቅሬታቸውን በቀን 02/07/2013 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ፤ በኪራይ በተሰጣቸው ቤቶች ውስጥ እየኖሩ መሆናቸውን በመጥቀስ፤ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ እንዲሁም ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ሲቆጥቡና ሲጠባበቁ ቆይተው የ13ኛው ዙር የኮንዶሚኒየም ቤት ባለ ዕድል መሆናቸውን ይጠቅሳል፡፡

ወደ ገጽ 7 ዞሯል


# ፍረዱኝ

# የጋራ መኖሪያ ቤት በማስተሳሰፍ...

ከገጽ 6 የዞረ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ግን ለመምህራን በኪራይ ስለሚቀርቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለማስተላለፍና ለማስተዳደር በወጣ መመሪያ ቁጥር 01/2011 መሠረት በክፍል አራት(4) በአከራይና ተከራይ መብትና ግዴታ በተዘረዘረው ቁጥር 20 ልዩ የተከራይ መብት ንዑስ ቁጥር 3 ላይ በተገለፀው መሠረት፤ መምህሩ የቤት ኪራይ ተጠቃሚ ሆኖ መንግሥት በዘረጋው የቤት ልማት ፕሮግራም በራሱ ወይም በትዳር አጋሩ ስም ቤት ዕጣ ከደረሰው ተመሳሳይ የቤት ዓይነት ከሆነና በኪራይ የያዙትን ቤት ከፈለጉ በወቅቱ በሚኖረው የቤት የማስተላለፊያ ዋጋ ግምት ተሰልቶ በረጅም ጊዜ ሽያጭ በስሙ እንዲተላለፍት ይደረጋል ይላል፡፡ይሁንና፤ በ13ኛው ዙር ቤት ደርሶን ቅያሬ በመጠየቅ በመመሪያው መሠረት መዋዋል ሲገባን ይህ አልሆነም፡፡

በመሆኑም በ13ኛው ዙር በቤት መተላለፊያ ዋጋ እንድንዋዋል መደረጉ መመሪያውን የጣሰ በመሆኑ፣ በተለያዩ ዙር የተላለፉ ቤቶችን በአንድ ዓይነት የመተላለፊያ ዋጋ እንድንከፍል መደረጋችን፤ ሙሉ ዕድሜውን በመምህርነት እስከ ጡረታ እያገለገለ ያለውን መምህር ተጠቃሚነት ያላገናዘበ እና በመመሪያ ተራ ቁጥር 20 ንዑስ ቁጥር 1 (አንድ) ከግምት ውስጥ ያላስገባ አሠራር እየተሠራ መሆኑ፤ ተመሳሳይ የቤት ዓይነት በተለዋጭ ተተክተው ለሌላ ለሚተላለፍለት ወገን የማስተላለፊያ ዋጋ እና እየኖርንበት ያለው የኮንዶሚኒየም የተላለፈበት ዋጋ ከግምት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ የከተማ አስተዳደሩ ለመምህራን በኪራይ ስለሚቀርቡ መኖሪያ ቤቶች በወጣው መመሪያ መሠረት እንዲያዋውለን እና በወቅቱ በሚኖረው የቤት የማስተላለፊያ ዋጋ እንድንከፍል ወይንም እንዲተላለፍልን የሚል ማመልከቻ በፊርማቸው አስደግፈው ለከተማው ቤቶች ኤጀንሲ ያስገቡ ሲሆን በግልባጭም ለአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ እና ለአዲስ አበባ መምህራን ማህበር አሳውቀዋል፡፡


1. አንቀጽ 20 ንኡስ አንቀጽ 1 «ተከራይ ሙሉ እድሜዉን በመምህርነት እስከ ጡረታ ካገለገለ እስከዚያ የከፈለዉ ኪራይ ታስቦ ባለዉ መደበኛ አሰራር የቀሪዉን የቤቱን ዋጋ በወቅቱ በሚኖረዉ የቤት ማስተላለፊያ ዋጋ ግምት ተሰልቶ በረጅም ጊዜ በሽያጭ ቤቱ ይተላለፍለታል» በሚለዉ መሰረት እየተሰራ መሆኑ፣
2. በዚሁ እንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 «መምህሩ በቤት ኪራይ ተጠቃሚ ሆኖ መንግስት በዘረጋዉ የቤት ልማት ፕሮግራም በራሱ ወይም በትዳር አጋሩ ስም የቤት እጣ ከደረሰዉ ተመሳሳይ የቤት ዓይነት ከሆነና በኪራይ የያዙትን ቤት ከፈለጉ በወቅቱ በሚኖረዉ የቤት ማስተላለፊያ ዋጋ ግምት ተሰልቶ በረጅም ጊዜ ሽያጭ በስሙ እንዲተላለፍለት ይደረጋል» በሚለው እና ባቀረባችሁት ጥያቄ መሰረት እንድትስተናገዱ የተደረገ ሲሆን በወቅቱ በሚኖረው የቤት ማስተላለፊያ ዋጋ ማለት አሁን ያለዉን ማለት ስሆን በዚህም መሰረት በ13ኛዉ ዙር የጋራ መኖሪያ ቤት በተወሰነዉ የካሬ ማስተላለፊያ ዋጋ መሰረት እንድትከፍሉ መደረጉ ትክክለኛ በመመሪያዉ እና በላዉ አሰራር መሰረት የተሰራና እየተሰራ ያለ መሆኑን እናሳዉቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ካሳሁን ዘውዴ ሁሪሳ
የጋራ መኖሪያ ቤቶች ማስተላለፍ
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ግልባጭ
- ለዋና ዳይሬክተር
- ለቤ/ማስ/አስ/ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር
- ለኮርፖሬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ
- ለጋራ መኖሪያ ቤት ማስተላለፍ ዳይሬክቶሬት
- ለጋራ መኖሪያ ቤት ማስተላለፍ ቡድን

ቤ/ል/ኮ

☎-0118-33-35-53 ዜጉችን የቤት ባለቤት በማድረግ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እናረጋ ግጣለን0118-12-23-65E-Mail

## ኮርፖሬሽኑ በደብዳቤ የሰጠው ምላሽ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን መምህራን ላቀረቡት ቅሬታ መጋቢት 29 ቀን 2013 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ቤ/ል/ኮ/ቁ1/19/ 8938 ለቀረበው ቅሬታ ከመመሪያ አንጻር መልስ መስጠትን ይመለከታል በሚለው ደብዳቤው፤ መምህራኑ በቀን 02/07/13 ዓ.ም በተጻፉት ማመልከቻ ከአሁን በፊት ለመምህራን መንግሥት ባመቻቸው ፕሮግራም በኪራይ የጋራ መኖሪያ ቤት አግኝተው እየኖሩበት መሆኑን በመግለፅ በጋራ መኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ተመዝግበው ሲጠባበቁ በ13ኛው ዙር ዕጣ ባለ እድል መሆናቸውን በመግለጽ ለመምህራን በኪራይ ስለሚቀርቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለማስተላለፍ እና ለማስተዳደር በወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2011 ክፍል 4 በአከራይና ተከራይ መብትና ግዴታ በተዘረዘረው ቁጥር 20 ልዩ የተከራይ መብት ንዑስ ቁጥር 3 ላይ በተገለጸው መሠረት፤ መምህሩ የቤት ኪራይ ተጠቃሚ ሆኖ መንግሥት በዘረጋው የቤት ልማት ፕሮግራም በራሱ ወይም በትዳር አጋሩ ሥም የቤት ዕጣ ከደረሰው ተመሳሳይ የቤት ዓይነት ከሆነና በኪራይ የያዙትን ቤት ከፈለጉ በወቅቱ በሚኖረው የጋራ መኖሪያ ቤት ማስተላለፊያ ዋጋ ግምት ተሰልቶ በረጅም ጊዜ ሽያጭ በስሙ እንዲተላለፍለት ይደረጋል ይላል፡፡ነገር ግን በ13ኛው ዙር ቤት ደርሶን ቅያሬ በመጠየቅ በመመሪያው መሠረት መዋዋል ሲገባን፡-

በ13ኛው ዙር የቤት ማስተላለፊያ ዋጋ እንድንዋዋል መደረጋችን መመሪያውን የጣለ በመሆኑ፤ በተለያዩ ዙሮች የተላለፉ ቤቶችን በአንድ ዓይነት የማስተላለፊያ ዋጋ እንድንከፍል መደረጋችን፤ ሙሉ ዕድሜውን በመምህርነት እስከጡረታ እያገለገለ ያለውን መምህር ተጠቃሚነት ያላገናዘበ እና መመሪያ ተራ ቁጥር 20 ንዑስ ቁጥር አንድን ከግምት ውስጥ ያላስገባ አሠራር እየተሠራ መሆኑ፤ ተመሳሳይ የቤት ዓይነት በተለዋጭ ተተክተው ለሌላ ለሚተላለፍለት ወገን የማስተላለፊያ ዋጋ እና እየኖርንበት ያለው ኮንዶሚኒየም የተላለፈበት ዋጋ ከግምት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ የከተማ አስተዳደሩ ለመምህራን በኪራይ ስለሚቀርቡ መኖሪያ ቤቶች በወጣው መመረያ መሠረት እንዲያዋውለን እና በወቅቱ በሚኖረው የማስተላለፊያ ዋጋ እንድንከፍል ስንል በሙሉ ድምፅ በፊርማችን በማረጋገጥ እናመለክታለን በማለት በጠየቁት መሠረት የሚከተለውን ምላሽ ሰጥቷል፡፡

ኮርፖሬሽኑ እንደሚለው፤ ጥያያቄዎቹ ሁሉም በአንድ ጉዳይ ላይ በወቅታዊ የጋራ መኖሪያ ቤት ማስተላለፊያ ዋጋ እንድንከፍል መደረጉ መመሪያ የጣሰ ሥራ ተፈጽሞብናል የሚል እና የመምህራንን ተጠቃሚነት ያላገናዘበ አሠራር እየተሠራ ነው የሚል ነው ሲል ያጠቃልለዋል፡፡ይሁንና ተቋሙ በመመሪያና አሠራር የሚመራ በመሆኑ በዚህም መሠረት በ13ኛው ዙር የጋራ መኖሪያ ቤት ዕጣ እድለኞች ሆነው በኪራይ ከያዙት ቤት ጋር ተመሳሳይ ለሆነ መምህራን በዕጣ የደረሰን ቤት ተመላሽ ተደርጎ በኪራይ የተሰጠን ቤት በመመሪያው መሠረት በሽያጭ ይተላለፍልን ብላችሁ ባቀረባችሁት ጥያቄ መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ለመምህራን በኪራይ ስለሚቅርቡ ቤቶች ለማስተላለፍና ለማስተዳደር በወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2011 ክፍል አራት መሠረት፤

አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 1«ተከራይ ሙሉ ዕድሜውን በመምህርነት እስከ ጡረታ ካገለገለ እስከዚያ የከፈለው ኪራይ ታስቦ ባለው መደበኛ አሠራር የቀሪውን የቤቱን ዋጋ በወቅቱ በሚኖረው የቤት ማስተላለፊያ ዋጋ ግምት ተሰልቶ በረጅም ጊዜ በሽያጭ ቤቱ ይተላለፍለታል» በሚለው መሠረት እየተሠራ መሆኑ፣ በዚሁ እንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 «መምህሩ በቤት ኪራይ ተጠቃሚ ሆኖ መንግሥት በዘረጋው የቤት ልማት ፕሮግራም በራሱ ወይም በትዳር አጋሩ ሥም የቤት ዕጣ ከደረሰው ተመሳሳይ የቤት ዓይነት ከሆነና በኪራይ የያዙትን ቤት ከፈለጉ በወቅቱ በሚኖረው የቤት ማስተላለፊያ ዋጋ ግምት ተሰልቶ በረጅም ጊዜ ሽያጭ በስሙ እንዲተላለፍለት ይደረጋል» በሚለው እና ባቀረባችሁት ጥያቄ መሠረት እንድትስተናገዱ የተደረገ ሲሆን በወቅቱ በሚኖረው የቤት ማስተላለፊያ ዋጋ ማለት አሁን ያለውን ማለት ሲሆን በዚህም መሠረት በ13ኛው ዙር የጋራ መኖሪያ ቤት በተወሰነው የካሬ ማስተላለፊያ ዋጋ መሠረት እንድትከፍሉ መደረጉ ትክክለኛ በመመሪያው እና ባለው አሠራር መሠረት የተሠራና እየተሠራ ያለ መሆኑን እናሳውቃለን ሲል ምላሽ ሰጥቷል፡፡

## ‹‹ፍትሃዊነት የጎደለው ምላሽ››

ምንም እንኳን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን መምህራን ላቀረቡት ቅሬታ መጋቢት 29 ቀን 2013 ዓ.ም ለቀረበው ቅሬታ ከመመሪያ አንጻር መልስ መስጠትን ይመለከታል በሚለው ደብዳቤው፤ ለሰጠው ምላሽ መምህራኑ በቀን 12/08/2013 ዓ.ም በፃፉት ደብዳቤ ‹‹ፍትሃዊነት የጎደለው ምላሽ›› ሲሉ አጣጥለውታል፡፡

ደብዳቤው ላቀረብነው አቤቱታ ፍትሃዊ ያልሆነ ምላሽ እና መሪያውን ያላገናዘበ መልስን ይመለከታል ሲል፤ ኮርፖሬሽኑ የሰጠው ምላሽ የመምህሩን ተጠቃሚነት ያላገናዘበ ከማንኛውም የቤት ተጠቃሚ ዜጋ የበለጠ እንዲከፍል መደረጉ፤ በዕጣ የደረሰንን ወይም ተመላሽ ያደረግነውን ቤት ኮርፖሬሽኑ ለሌላ የሚያስተላልፍበት የቤት ዋጋ እና በመመሪያው መሠረት በቅያሬ ያገኘነውን ቤት አሁን ባለው የቤት ማስተላለፊያ ዋጋ ማዋዋሉ በሕግ አግባብ ትክክል አለመሆኑን ጠቁመዋል፡፡በተጨማሪም እስከአሁን ስንከፍለው የነበረው አለመያዙ በራሱ መምህሩን ተጠቃሚ ያላደረገ እና ዕጣው የወጣው ከመሪያው በኋላ መሆኑ በአጠቃላይ መምህሩን ተጠቃሚ ያላደረገ እንዲያውም ተጎጂ በማድረጉ መምህራን ማኅበሩም ሆነ ትምህርት ቢሮው ለተሰጠው መልስ በጥንቃቄ እንዲያየው አሳስበዋል፡፡

## የካቢኔ ውሳኔ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ15ኛው መደበኛ ስብሰባ ቀደም ሲል ለመምህራን በኪራይ የተላለፉ የጋራ መኖሪያ ቤቶች በሽያጭ እንዲተላለፍላቸው ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት ተግባራዊ ለማድረግ ከትምህርት ቢሮ አመራርና ባለሙያዎች፤ ከመምህራን ማህበር ተወካዮችና ከቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን አመራርና ባለሙያዎች በቀን 11/01 2014 ዓ.ም የተደረገ ቃለ ጉባዔ እንደሚከተለው ሰፍሯል፡፡

የከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ለመምህራን በኪራይ ተሰጥቶ የነበረ ቤት በሽያጭ እንዲተላለፍላቸው ከወሰነበት ቀን ጀምሮ የሽያጭ ውል እስከሚጠናቀቅበት ቀን ድረስ በጡረታ የሚገለሉ መምህራን ኪራይ የከፈሉት ገንዘብ ታስቦላቸው በ2009 ዓ.ም በነበረው የ20/80 የጋራ መኖሪያ ቤት ማስተላለፊያ ዋጋ መሠረት ይስተናገዳሉ፡፡ በሹመት ከመምህርነት ሥራ የለቀቁ መምህራን ሹመት ላይ ስለመሆናቸው ከፓርቲ ጽሕፈት ቤትና ከትምህርት ቢሮ ማረጋገጫ ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው ይላል፡፡

የቤቶቹ የማስተላለፊያ ዋጋም በካቢኔው ውሳኔ መሠረት የ2009 ዓ.ም የ20/80 የጋራ መኖሪያ ቤት ማስተላለፊያ ዋጋ ሆኖ፤ ለስቱዲዮ 2483 በካሬ ሜትር፣ ለባለ አንድ 3438 በካሬ ሜትር እና ለባለ ሁለት መኝታ 4394 በካሬ ሜትር ይሆናል፡፡ይሁንና በአሠራር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከሁለቱ ተቋማት የተውጣጡ ኮሚቴዎች በማደራጀት ለትምህርት ቢሮና ለቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ኃላፊዎች አቅርቦ ውሳኔ እንዲሰጥበት ይደረጋል ሲል አስቀምጧል፡፡

## መመሪያው ምን ይላል?

ለመምህራን በኪራይ ስለሚቀርቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለማስተላለፍና ለማስተዳደር የወጣ መመሪያ ቁጥር 01/2011 የአከራይና ተከራይ መብትና ግዴታ አንቀጽ 20 ልዩ የተከራይ መብት በሚለው ሥር የተቀመጡ ዝርዝር አስረጂዎች መካከል፤ ተከራይ ሙሉ ዕድሜውን በመምህርነት እስከ ጡረታ ካለ እስከዚያ የከፈለው ኪራይ ታስቦ ባለው መደበኛ አሠራር የቀሪውን የቤቱን ዋጋ በወቅቱ በሚኖረው የቤት ማስተላለፊያ ዋጋ ግምት ተሰልቶ በረጅም ጊዜ ሽያጭ ቤቱ ይተላለፍለታል ይላል፡፡

በሁለተኛው ተራ ቁጥር ደግሞ ተከራይ በመምህርነት እያገለገለ እያሉ በሞት ቢለዩ በዚህ አንቀጽ ንፁስ አንቀጽ አንድ በተገለፀው አግባብ የትዳር አጋር እና ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ልጆች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል ሲል ያስቀምጣል፡፡እንዲሁም መምህሩ የቤት ኪራይ ተጠቃሚ ሆኖ መንግሥት በዘረጋው የቤት ልማት ፕሮግራም በራሱ ወይም በትዳር አጋሩ ሥም የቤት ዕጣ ከደረሰው ተመሳሳይ የቤት ዓይነት ከሆነና በኪራይ የያዙትን ቤት ከፈለጉ በወቅቱ በሚኖረው የቤት የማስተላለፊያ ዋጋ ግምት ተሰልቶ በረጅም ጊዜ ሽያጭ በስሙ እንዲተላለፍለት ይደረጋል፡፡በተጨማሪም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንጽ 3 ቀደም ሲል ተከራይ በኪራይ የያዘውን ቤት በረጅም ጊዜ ሽያጭ በሥሙ እንዲተላለፍለት ከተደረገ አከራይ ተመሳሳይ የቤት ዓይነት በተለዋጭ የሚተካ ይሆናል ሲል መመሪያው በግልፅ አስቀምጧል፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

# «ለሁሉም ጊዜ አለው፤»

ትውልድ ቢሔድ ቢመጣ ዘመን የማይሽረው ወርቅ የጠቢቡ ይትበሀል አለ። «ለሁሉም ጊዜ አለው፤» የሚል። ዘመን ተሻጋሪ። ዛሬም ያልጨረተ። ሕያው። በታላቁ ቅዱስ መጽሐፍ መክብብ 3:1-8 ላይ ደግሞ፤«ለሁሉም ነገር ጊዜ አለው፤ ከሰማይ በታች ለሚከናወነው ለማንኛውም ነገር ወቅት አለው፤ ለመወለድ ጊዜ አለው፤ ለመሞትም ጊዜ አለው፤ ለመትከል ጊዜ አለው፤ ለመንቀልም ጊዜ አለው፤ ለመግደል ጊዜ አለው፤ ለማዳንም ጊዜ አለው፤ ለማፍረስ ጊዜ አለው፤ ለመገንባትም ጊዜ አለው፤ ለማልቀስ ጊዜ አለው፤ ለመሣቅም ጊዜ አለው፤ ለኀዘን ጊዜ አለው፤ ለጭፈራም ጊዜ አለው፤ ድንጋይ ለመጣል ጊዜ አለው፤ ድንጋይ ለመሰብሰብም ጊዜ አለው፤ ለመተቃቀፍ ጊዜ አለው፤ ለመለያየትም ጊዜ አለው፤ ለመፈለግ ጊዜ አለው፤ ለመተው ጊዜ አለው፤ ለማስቀመጥ ጊዜ አለው፤ አውጥቶ ለመጣልም ጊዜ አለው፤ ለመቅደድ ጊዜ አለው፤ ለመስፋትም ጊዜ አለው፤ ለዝምታ ጊዜ አለው፤ ለመናገርም ጊዜ አለው፤ ለመውደድ ጊዜ አለው፤ ለመጥላትም ጊዜ አለው፤ ለጦርነት ጊዜ አለው፤ ለሠላምም ጊዜ አለው።»ይለናል።

ይህ ታላቅ ቃል ተገቢውን ጊዜ መርጦ ማድረግ ወይም "ታይሚንግ/timing"ለሕዝበ አዳም ስጋም ሆነ ነፍስ አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል። በተለይ ለመሪነት ወይም ለአመራር ደግሞ እስትንፋስ ነው ማለት ይቻላል። የአንድን መሪ ስኬት ወይም ውድቀት የመበየን አቅም እንዳለው የዘርፉ ልሒቃን አጽንኦት ይሰጣሉ። ታይሚንግ ተገቢውንና ትክክለኛውን ጊዜ መርጦ የመወሰን ወይም ለድርጊት የመነሳት ችሎታ ነው። በእጅ የገባን መልካም አጋጣሚን ሳያባክኑ መጠቀምም ነው። ከዚህ በተጨማሪ ለውጥን ለመተግበር ፣ ትክክለኛውን መልዕክት በትክክለኛው ጊዜ ለማስተላለፍ ወይም ለተግባቦት ፣ ለቀውስ አመራር ፣ መሪው በስሩ ካሉ አመራሮች ጋር ሳይቀር ለመነጋገርና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ጣልቃ ለመግባት ታይሚንግ ወሳኝ ነው። በአጠቃላይ ታይሚንግ የተዋጣለት መሪ መለያ ነው።

ስለ ታይሚንግ ይህን መንደርደሪያ እንዳነሳ በተለይ ያስገደደኝ ሰሞነኛው የባሕር በር ጥያቄ ነው። 120 ሚሊዮን ሕዝብ ላለውና ከ1.1ሚሊዮን ስኩየር ኪሜ ስፋት ለሚያካልል እና በአመት ከ2 ቢሊዮን ዶላር በላይ ለወደብና ለኪራይ ለሚያወጣ ፤ ለእልፍ አእላፍ አመታት ባለወደብ ለነበረ ሀገር የወደብ ጉዳይ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ቀዳሚ አጀንዳም ነው። ጥያቄው ይሄን አንገብጋቢ አጀንዳ ወደፊት የአመጣንበት ታይሚንግ ተገቢ ነው የሚለው ነው። እንደ ዳያ ነቃይ የፊት የፊቱን እንዲሉ ሌሎች የባሱ የፊት የፊት አጀንዳዎች የሉንም ወይ። ሠላምና ደህንነት፣ የኑሮ ውድነት፣ ሀገራዊ ምክክር፣ የሽግግር ፍትሕ፣ ወዘተረፈ ውዝፍ አጀንዳዎች ከፊት እያሉ በአናቱ የወደብን ጉዳይ የማምጣት ታይሚንግ ትክክል ነው ስል እጠይቃለሁ። እስኪ ሃሳብ እንሰናዘርበት።

በነገራችን ላይ የሀገራችን ባሕር በርና ወደብ አልባ መሆኗ እንደ እግር እሳት ከሚያንገበግባቸው ዜጎች አንዱ ነኝ። ደርግን ፣ ሕወሓትንና ሻዓብያን እንዲሁም ታሪካዊ ጠላቶቻችን ከዚህ ታላቅ ደባ ጀርባ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ስላሉበት ፖለቲካዊ ነፍስ ካወቅሁበት ጀምሮ እንዳወግዝኋቸው አለሁ። በተቀረው አጀንዳ ሆኖ የሚነሳበት ትክክለኛ ጊዜው መቼ ነው ከሚለው ውጪ የባሕር በር ወይም የወደብ ጉዳይ ሀገራዊ አንገብጋቢ አጀንዳ መሆኑን እገነዘባለሁ። ሆኖም ያለንበት ሁኔታ ጥያቄው የሚነሳበት ትክክለኛ ጊዜ ነው ወይ ስል እጠይቃለሁ። ነገርን ነገር ያነሳዋልና ከዚህ ሰሞነኛ ጉዳይ ጋር ተያይዞ በአማርኛው የሪፖርተር ጋዜጣ ላይ የተነሱ ሃሳቦችን ላካፍላችሁ።

ዮናስ አማረ ባለፈው እሁድ ለንባብ በበቃው የአማርኛ ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ባስነበቡን መጣጥፍ የቅርብ ታሪካዊ ዳራውን በማንሳት ይጀምራል። የኤርትራን ዕጣ ፈንታ የሚወስነው ሕዝበ ውሳኔ ሊካሄድ በዋዜማው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ተቃውሞ ማስነሳታቸው ይታወሳል። እ.ኤ.አ. ጃኑዋሪ 4 ቀን 1993 በሺህ የሚቆጠሩ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች አደባባይ ወጥተው ታላቂቱን ሀገር ኢትዮጵያ የሚከፋፍልና ወደብ አልባ ሀገር የሚያደርግ ነው ያሉትን የኤርትራን መገንጠል በመቃወም መውጣታቸው አይዘነጋም። የጊዜው መንግሥት ለዚህ ተቃውሞ የሰጠው ምላሽ ጠንከር ያለ ነበር። በመቶዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎች የፀጥታ ኃይሎች በወሰዱት ዕርምጃ ቆሰሉ። ሁለት ተማሪዎች በሆስፒታል እንዳሉ መሞታቸውም ተረጋገጠ።

ኢትዮጵያ የባሕር በር አልባ ሀገር እንዳትሆን የሚለው የብዙ ዜጎች ጩኸት ሰሚ አጥቶ ቀረ። የኤርትራ መገንጠል ጉዳይ አፍጥጦ መጣ። ግንቦት 16 ቀን 1985 ዓ.ም. በተካሄደ ሪፈረንደም ኤርትራ ሉዓላዊት ሀገር ሆነች። ከኤርትራ ሕዝበ ውሳኔ ጎን ለጎን ይነሳ የነበረው የባሕር በር ወይም የወደብ ጥያቄም በጊዜው በነበረው መንግሥት ሆን ተብሎ ወደ ጎን መገፋት መጀመሩን ብዙዎች ያስታውሱታል። የታሪክ ምሁሩ ዳግማዊ ተስፋዬ (ዶ/ር) ከ1985 እስከ 1992 ዓ.ም. በነበሩት ዓመታት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ልሂቃን፣ እንዲሁም በአካዳሚክ ማኅበረሰቡ ዘንድ በባሕር በር ጉዳይ ከፍተኛ ውይይቶችና ክርክሮች ይደረጉ እንደነበር ያስታውሳሉ። ነገር ግን ይህንን ሁኔታ ያልወደደው የጊዜው አስተዳደር ሆን ብሎ በሚመስል መንገድ እነዚህን ውይይቶች እንዲዳፈኑ አድርጓል ይላሉ።

በጊዜው የነበረው ሥርዓት ከፍተኛ ባለሥልጣን የነበሩት ሌተና ጄኔራል አበበ ተክለ ሃይማኖት እ.ኤ.አ. በ2007 «Ethiopian's Sovereign Right of Access to the Sea Under International Law» በሚል ርዕስ ባሳተሙት መመረቂያ ጽሑፍ፣ የባሕር በር ጉዳይ ወደ ጎን የተገፋበትን መነሻ ምክንያት በሰፊው አብራርተዋል። «የገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል እስከ 1994 ዓ.ም. ነበርኩ። የጦሩ ከፍተኛ አመራር እንደመሆኔ መጠን መንግሥት በባሕር በር ጉዳይ ላይ ያለውን አቋም በቅርበት ማወቅም ነበረብኝ። በጊዜው የባሕር በር ጥያቄን በተመለከተ የተለየ ምስጢራዊ አቋም አልነበረንም።

የእኛ ዋናው ትኩረት ኢትዮጵያ የባሕር በር ጉዳይን ረስታ፣ ተጨባጩን ሀቅ ተቀብላ ሠላም በመገንባትና ድህነትን በማጥፋት ላይ ብታተኩር ይሻላል የሚል ነበር። «በጊዜው እኔም ሆነ ብዙዎቹ በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ያሉ ባለ ሥልጣናት የባሕር በር ጉዳይን ማንሳት፣ ከአዲሱ ሕገ መንግሥታችን ጋር የሚጋጭ ነው ብለን እናስብ ነበር። የባሕር በር ጥያቄ የሚያነሱት ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 39 የደነገገውን የብሔር ብሔረሰቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት የሚቃወሙ ናቸው ብለን እናስብ ነበር።

«የኤርትራን ነፃነት የማይቀበሉ ያለፈው የፊውዳላዊና የወታደራዊ ሥርዓት ናፋቂዎች ናቸው። የባሕር በር ጥያቄ የሚያነሱት የሚል አመለካከት ነበረን። ኢትዮጵያ የባሕር በር ወይም ወደብ ሊኖራት ይገባል የሚሉ ወገኖችን ፍፁም ስቃወም ነበር የኖርኩት፤» በማለት ሌተና ጄኔራል አበበ በዚህ ጥናታቸው አስፍረዋል። ልክ እንደዚህ ወደ ጎን ሲገፋ የቆየው የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ ከኤርትራ መገንጠል ጋር ተያይዞ ጠንከር ብሎ ቢነሳም፣ መንግሥት ጉዳዩ አይነሳብኝ በማለቱ ከውይይት መድረኮች ርቆ መቆየቱ ይታወሳል። ከ40 ያላነሱ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን በ1985 ዓ.ም. ከሥራ መባረራቸው መንግሥት በአካዳሚክ ማኅበረሰቡ ዘንድ የባሕር በር ጉዳይ እንዳይነሳ በመፈለጉ እንደሆነ ይወሳል። በዚህ ጊዜ የኤርትራ ሕዝበ ውሳኔ እንደሚካሄድ፣ እንዲሁም የባሕር በር ጥያቄ ገፍቶ እንደ መምጣቱ የመንግሥት ዕርምጃ ይህንኑ ፀጥ ለማሰኘት ያለመ ነበር የሚል ግምት አስነስቶ አልፏል።

የኤርትራ መገንጠል ኢትዮጵያ የባሕር በር አልባ አድርጓታል ቢባልም፣ ኢትዮጵያ በኤርትራ ወደቦች በነፃነት መገልገል እንደቀጠለች ታሪክ ያወሳል። በተመድ ሪሊፍ ዌብ በተባለ ድረ ገጽ ላይ የሠፈረው፣ «Eritrea – Ethiopia: IRIN Focus on Assab, 5 June 2000» በሚል ርዕስ የቀረበው ሀተታ ኢትዮጵያ በአሰብ ወደብ ከቀረጥና ከታሪፍ ነፃ በሆነ መንገድ መጠቀም መቀጠሏን ያወሳል። ስትገነጠል ለኢትዮጵያ አሰብ ወደብን በነፃነት እንድትገለገልበት ፈቅዳ የነበረችው ኤርትራ፣ በሒደት ግን ከጎረቤቷ ጋር አለመስማማት ውስጥ እንደገባች ተጠቅሷል። ለሁለቱ ተጎራባቾች አለመግባባት ምንጭ የነበሩት ደግሞ የወደብ አስተዳደር ጉዳይ፣ የኮሚሽን ክፍያና የመገበያያ ገንዘብ ጉዳይ እንደነበሩ ተመላክቷል። የሁለቱ ተጎራባቾች ውዝግብ በሒደት መካረሩንና ወደ ድንበር ጦርነት መሸጋገሩን ዘገባው ያትታል። ከድንበር ጦርነቱ በፊት ለኢትዮጵያም ሆነ ለራሷ ለኤርትራ ከፍተኛ የባሕር ንግድ መተላለፊያ በር የነበረው አሰብ ወደብ በሒደት ጥቅም አልባ ወደመሆን መሸጋገሩን ይህ ዘገባ ጨምሮ ያብራራል።

ኤርትራ ነፃ ሀገር ስትሆን የአሰብ ወደብ 70 በመቶ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። ኢትዮጵያ ወደቡን ላለመጠቀም ወስና ወደ ጂቡቲ ወደብ ፊቷን ስታዞር ግን ይህ ሁኔታ መቀየሩ ይነገራል። ሁለቱ ሀገሮች ወደ ጦርነት ሲገቡ ደግሞ አንዱ የሌላውን ሀገር ዜጋ በማስወጣቱ ከአነስተኛ ንግድ እስከ የወደብ አገልግሎት ሥራዎች ተሰማርተው የቆዩ አሰብ ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዕጣ ፈንታም መፈናቀል መሆኑ ተነግሯል። የኤርትራ ሰዎች ለወደብ አገልግሎቱ ይከፈለን የሚሉት ኮሚሽን እየጨመረ መምጣቱ እንደ ችግር ተነስቷል። የመገበያያ ገንዘባቸውን ወደ ናቅፋ በመቀየር የንግድ ሚዛንን ለማስቀየር መሞከራቸውም ሌላው እንቅፋት ተብሏል። በሌላ በኩል አንዲት ፍሬ ቡና ሳያመርቱ የኢትዮጵያን ቡና በርካሽ እየገዙ ከአፍሪካ ቀዳሚ የቡና ላኪ ሀገሮች ተርታ ለመሰለፍ መሞከራቸው ልዩነቱን የሚያሰፋ ብልጣ ብልጥ ዕርምጃ በሚል ይነገራል።

ዘገባው እንደሚለው ኮሚሽን የሚቀበሉበትን የወደብ መሠረተ ልማት ኢትዮጵያ በራሷ ወጪ ልታድስ ይገባል የሚል አቋም ኤርትራውያኑ ይዘው ነበር። በሌላ በኩል በሶቪየት ኅብረት ድጋፍ ተገንብቶ በነበረው የድፍድፍ ነዳጅ ማጣሪያ አጠቃቀም ላይ ጥያቄ መፈጠሩ ይነገራል። ለኤርትራም ሆነ ለኢትዮጵያ አገልግሎት ይሰጥ የነበረውንና የጋራ ሀብት ሆኖ የሚታየውን የነዳጅ ማጣሪያ ኢትዮጵያ በራሷ ወጪ ታድስ መባሉ የሁለቱን ሀገሮች ግንኙነት ካሻከሩ ምክንያቶች እንደ አንዱ ይወሳል። በዚህ ሁሉና በሌሎችም ተደራራቢ ምክንያቶች ወደ ጦርነት የገቡት ኤርትራና ኢትዮጵያ ከጦርነቱ በኋላ መልሰው ጉርብትናቸውን ለማደስ በመቸገራቸው የኢትዮጵያ የወደብ አገልግሎት አማራጭ በጂቡቲ ላይ ብቻ የተገደበ ሆኖ እንደቆየ ይነገራል። የታሪክ ምሁሩ ዳግማዊ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ ታኅሣሥ 3 ቀን 1993 ዓ.ም. አልጀርስ የተፈረመው የሠላም ስምምነት የኢትዮጵያን የወደብ ጥያቄ ጉዳይ የተከደነ አጀንዳ እንዳደረገው ይናገራሉ። ከሺህ ዓመታት በላይ ወደብ አጥታ የማታውቀዋ ኢትዮጵያ «የወደብ አልባነት ክስተት ገጠማት» ሲሉ ያስረዳሉ።

አክሱም የአዱሊስ ወደብን በ702 ዓ.ም. በዓረቦች ወረራ በማጣቷ መዳከሟን ያነሱት ምሁሩ፣ ሆኖም በመካከለኛው ዘመን ሀገሪቱ እንደዘይላ ባሉ ወደቦች መገልገሏን ያወሳሉ። ይህ ሁሉ አልፎ ከኢትዮ ኤርትራ ጦርነት በኋላ ሀገሪቱ መልሳ ወደብ አልባ መሆኗ በብዙ መንገድ ለጉዳት እንደዳረጋት ነው የሚናገሩት። የገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስትሩ አሕመድ ሽዴ እ.ኤ.አ. ጁላይ 16 ቀን 2013 ላይ ለወደብ ኪራይ ሀገሪቱ በቀን ሁለት ሚሊዮን ዶላር ትከፍላለች ማለታቸውን ያስታውሳሉ። በዓመት እስከ ሁለት ቢሊዮን ዶላር አሁን ድረስ ታወጣለች መባሉንም ተጨማሪ የጉዳት ማሳያ አድርገው አስቀምጠውታል።

የዓለም አቀፍ ሠላም ጥናት መምህሩ አቶ ጋረደው አሰፋ በበኩላቸው፣ ‹ኢትዮጵያ እንደ አሰብ ባሉ ወደቦች ካልተጠቀመች ወደቡ የግመል መጠጫ ይሆናል› በሚል የተንሸዋረረ ዕይታ መሪዎቿ ታላቂቱን ሀገር ወደብ አልባ አድርገዋት መኖራቸውን ይናገራሉ። ኢትዮጵያ የባሕር በር አልባ ሀገር መሆኗ ሀገራዊ የሥነ ልቦና መቃወስን የፈጠረ ጉዳይ መሆኑንም ይገልጻሉ። ወደብ አልባ መሆን ከሥነ ልቦና አልፎ ዲፕሎማሲያዊ መሽመድመድንም በኢትዮጵያ ላይ ያስከተለ ስለመሆኑ አስረድተዋል።

በ1985 ዓ.ም. የተመድ ዋና ጸሐፊ ግብፃዊው ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊ ኤርትራን ለማስገንጠል አዲስ አበባ ሲገቡ ለተቃውሞ አደባባይ ከወጡት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መካከል ሰባት ተማሪዎችን መግደሉና ብዙዎችን ማቁሰሉ የሚነገረው የያኔው የኢትዮጵያ መንግሥት፣ በወደብ ጉዳይ አንዳችም ምክረ ሃሳብም ሆነ ተቃውሞ እንደማይሻ ቁርጥ አቋም የያዘ ይመስል ነበር ይባላል። 'በጂቡቲ ላይ ብቻ ጥገኛ ሆነን እንዴት ልንዘልቀው ነው' የሚሉ ድምፆች መስሚያ አልነበራቸውም ይባላል።

የጊዜው መንግሥት በወደብ ጉዳይ የሚነሱ ሃሳቦችንም ሆነ ሃሳብ ሰጪዎችን በቀናነት መመልከት የተወ እንደነበር ታሪክ ከትቦታል። ሌላው ቀርቶ ስለቀይ ባሕር የተሠሩ ፊልሞች ከመድረክ እንዲወርዱ መደረጉ ይነገራል። በአርቲስት ጥላሁን ጉግሳ የተሠራው ፊልም የገጠመው ዕጣ ይህ ነበር ይባላል። ድምፃዊ ቴድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) በ1997 ዓ.ም. በሠራው አልበም ውስጥ ያካተተው ‹ካብ ዳህላክ› ሙዚቃ ሕዝብ ቢወደውም የወቅቱን አገዛዝ ክፉኛ ያበሳጨ እንደነበር ይነገራል።

የኢሕአዴግ አስተዳደር የባሕር በር ጉዳይ አይነሳ ቢልም ጉዳዩ ጭርሱን ተዳፍኖ አለመቅረቱ ይነገራል። ታሪክን፣ ጂኦግራፊን፣ ኢኮኖሚንም ሆነ ጂኦ ፖለቲካዊ መነሻ ነጥቦችን ተመርኩዘው የባሕር በርና የወደብ አስፈላጊነትን በየጊዜው ለመተንተን የሞከሩ ወገኖች ግን ኢትዮጵያ በኪራይ ወደብ ያውም በጂቡቲ ላይ ብቻ ጥገኛ ሆና መዝለቁ እንደሚከብዳት ለረጅም ጊዜ ሲወተውቱ ቆይተዋል። ከጂቡቲ ጋር 349 ኪሎ ሜትር ድንበር የምትጋራው ኢትዮጵያ፣ ከኤርትራ ጋር 912፣ ከኬንያ 861፣ ከሶማሊያ 1,600፣ ከሱዳን 744፣ እንዲሁም ከደቡብ ሱዳን ጋር 1,114 ኪሎ ሜትር የድንበር መስመሮችን የምትጋራውና ምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ ለሚባለው ቀጣና እምብርት የሆነችው ኢትዮጵያ ያለ ወደብ መቅረቷ ብዙ ሀገር ወዳድ ዜጎችን ሲያሳስብ የቆየ ጉዳይ እንደነበር ይታወቃል።

ኢትዮጵያ በየቀኑ ከ3.3 ሚሊዮን በላይ በርሜል ነዳጅ ዘይት ለሚተላለፍበትና የዓለማችን ወሳኝ ንግድ መስመር ለሆነው ለቀይ ባሕር ቀጣና የቅርብ ሩቅ ሆና መኖሯ ቢዳፈንም፣ ውስጥ ውስጡን ሲብላላ የቆየ ጉዳይ ነበር ይባላል። በየቀኑ ከ160 በላይ ግዙፍ የንግድ መርከቦች የሚቀዝፉበት ቀይ ባሕር ከ700 ቢሊዮን ዶላር በላይ የዓለም ዓመታዊ ንግድ ልውውጥ የሚካሄድበት ነው። የስዊዝ ቦይና የሕንድ ውቅያኖስ መገናኛ የሆነው ቀይ ባሕር የእስያንና የአፍሪካ አኅጉራትን ከአውሮፓ አኅጉራት ጋር የሚያስተሳስር የዓለም ቁልፍ የንግድ መስመርም ነው።

ሻሎም ! አሜን።

# የሀገሪቱን የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ አቅም ያሳየው የንግድ ትርኢት

**ፍሬሕይወት አወቀ**




**የንግድ ትርዒቱ በተከፈተበት ወቅት፤**

ሀገራት የተለያዩ አላማዎችን ታሳቢ ያደረጉ ኤግዚቢሽንና ባዛሮችን በማካሄድ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችን ያገኛሉ። ኤግዚቢሽንና ባዛሮቹ በዋናነት የገበያ ትስስርን በመፍጠር፣ የልምድ ልውውጥ በማድረግና በሀገር ውስጥ ያለውን የቴክኖሎጂና የምርት አቅም ለመረዳት ያግዛሉ። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቶችን ማካሄድ አበርክቶው የጎላ ነው። አምራቾች ምርቶቻቸውን ከማስተዋወቅና የገበያ ትስስር ከመፍጠር ባለፈ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የልምድ ልውውጥ ማድረግ የሚችሉበትን ዕድል ይፈጥራሉ።

ለዚህም በቅርቡ በአዲስ አበባ ከተማ ስካይ ላይት ሆቴል ለአራት ቀናት የተካሄደው ዘጠነኛው የአፍሪካ ሶርሲንግ እና የፋሽን ሳምንት (ASFW) ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት አንዱ ማሳያ ነው። ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ የአፍሪካ የቆዳ፣ የጨርቃ ጨርቅ፣ አልባሳት እና ፋሽን ኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ ውጤቶች ለዕይታ የቀረቡበት የንግድ ትርዒት እና ኮንፍረንስ ነው። መድረኩ በርካታ የገበያ ዕድሎችን በመፍጠር ረገድ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲሁም የልምድ ልውውጥ የሚደረግበት እንደሆነም ተነግሮለታል።

የንግድ ትርዒቱ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ታምርት ፕሮጀክት አስተባባሪና ከትሬድ ፌርስ ግሩፕ ጋር በትብብር የተዘጋጀ ነው። ላለፉት ስምንት ጊዜያት በተካሄደበት ወቅትም መሻሻል እየታየበት የመጣ ስለመሆኑ በመድረኩ ላይ  የተጠቆመ ሲሆን፣ በተለይም ለሀገር ውስጥ አምራቾች ሰፊ የገበያ ዕድል እየፈጠረ ያለና አምራቾቹ ለምርቶቻቸው አስፈላጊ ግብዓቶችን የሚያገኙበት እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያደርጉበትና ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት መሆኑም ተመላክቷል።

በንግድ ትርዒቱ ከተሳተፉት የሀገር ውስጥ አምራቾች መካከል የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ እህት ኩባንያ የሆነው ኢትዮ ሌዘር ኢንዱስትሪ /ኤሊኮ/ አንዱ ነው። የኤሊኮ ማርኬቲንግ ማናጀር ወይዘሮ ኢትዮጵያ ታደሰ፤ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ ለገበያ ትስስርና ለቴክኖሎጂ ሽግግር እጅግ ጠቃሚ መሆኑን ገልጻለች።

ወይዘሮ ኢትዮጵያ እንዳለችው፤  ኢትዮ ሌዘር /ኤሊኮ/ ከ75 ዓመት በላይ የቆየ አንጋፋ ድርጅት ነው። በውስጡም ሁለት የቆዳ ፋብሪካዎች፣ ሁለት የጫማ ፋብሪካዎችና አንድ የቆዳ ውጤቶች ማለትም ጃኬት፣ ቦርሳና የመሳሰሉትን የሚያመርት ፋብሪካ ይዟል።

ድርጅቱ አጠቃላይ የቆዳ ውጤቶችን አምርቶ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እያቀረበ ይገኛል። ከሚያቀርባቸው ምርቶች መካከል ያለቀለት ብትን ቆዳን ጨምሮ ቦርሳ፣ ጫማና ቀበቶ ይገኙበታል። ትልቁን የገበያ ድርሻ የሚወስደው የውጭ ገበያ ሲሆን፤ በተለይም ብትን ቆዳ በስፋት ለውጭ ገበያ ያቀርባል። የኢትዮጵያ የቆዳ ምርቶች በውጭ ገበያ እጅግ ተፈላጊ ሲሆኑ፣ ድርጅቱ ምርቶቹን ከሚልክባቸው ሀገሮች መካከል የአፍሪካ ሀገራት፣ አሜሪካ፣ ጣሊያን፣ ህንድ፣ ቻይና ይጠቀሳሉ።

‹‹ከቆዳ ውጤቶች በበለጠ ብትኑ ቆዳ በውጭ ገበያ ይመርጣል›› የምትለው ማርኬቲንግ ማናጀሯ፤ ለዚህም ዋናው ምክንያት የጫማ ሶልን ጨምሮ የተለያዩ ግብዓቶች /አክሰሰሪዎች/ በሀገር ውስጥ ባለመኖራቸው እንደሆነ ነው ያመላከተችው። በዚህ የተነሳም የቆዳ ውጤቶቹን የውጭ ገበያው በሚፈልገው ጥራት ልክ ማምረት አለመቻሉን ጠቅሳ፣ በዚህ ምክንያት ሀገሮቹ ብትኑን ቆዳ ወስደው እንደፈለጉ ያመርቱበታል ብላለች።

ጫማ፣ ቦርሳ፣ ቀበቶና ሌሎች የቆዳ ውጤቶች ሰፊ ገበያ ያላቸው በሀገር ውስጥ መሆኑን ጠቅሳ፣ በዓለም ገበያ ተወዳድሮ ለመግባት ቴክኖሎጂውን መጠቀምና የተለያዩ የምርት ማጠናቀቂያ ግብዓቶችን ማግኘት የግድ መሆኑን ጠቁማለች። ለዚህም እንዲህ ዓይነት ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቶች እንደሚጠቅሙ ነው የገለጸችው። በንግድ ትርዒቱ ላይ የገበያ ትስስር ከመፍጠር ባለፈ ከአክሰሰሪ አስመጪ ኩባንያዎች ጋር የመተዋወቅና የልምድ ልውውጥ የማድረግ ዕድል እንዳለና ይህም ለሀገር ውስጥ ምርቶች በእጅጉ እንደሚጠቅም ተናግራለች።

በከበሩ ማዕድናት የተለያዩ ጌጣጌጦችን አምርቶ ለገበያ የሚያቀርበው ሎላይስ ጀምስቶን  ሌላው በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ የተሳተፈ ድርጅት ነው። ድርጅቱ እነዚህን ምርቶቹን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እንደሚያቀርብ የድርጅቱ የማርኬቲንግ ባለሙያ ወጣት ኪያ ሞሲሳ ትናገራለች።  የአንገት ጌጥ፣ የጆሮ ጌጥ፣ ብራስሌት፣ የአንገት ሃብልና የተለያዩ ቀለበቶችን ከከበሩ ድንጋዮች አምርቶ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ያቀርባል ስትል ታብራራለች።

እሷ እንደምትለው፤ የከበሩ ማዕድናቱ ከሀገር ውስጥ የሚያገኙ ሲሆን፤ ድርጅቱ በተለይም ከወሎ፣ ከደላንታና ከአክሱም ከሚያመጡ አቅራቢዎች ያገኛል። ድርጅቱ ሁሉንም ዓይነት የከበሩ ድንጋዮችን ይጠቀማል፤ በተለይ ኦፓል የተባለውን የከበረ ድንጋይ በስፋት የሚጠቀም ሲሆን፣ የዚህ የከበረ ድንጋይ ምርቶች ሰፊ ገበያ አላቸው። ምርቶቹ በአብዛኛው ለውጭ ገበያ ይቀርባሉ፤ በአውሮፓና አሜሪካ ሰፊ ገበያ እንዳለው ወጣት ኪያ ገልጻ፤ አሁን አሁን የከበሩ ማዕድናት ከውጭ ገበያ በተጨማሪ በሀገር ውስጥ ገበያም እየተለመደ መምጣታቸውን አመልክታለች።

ማህበረሰቡ ቀደም ሲል ለማዕድን ብዙም ትኩረት ይሰጥ እንዳልነበር ያስታወሰችው ኪያ፤ መንግሥት ለማዕድን ዘርፉ በሰጠው ትኩረት በተለይም ማዕድን ሚኒስቴር በሚያዘጋጃቸው ኤግዚቢሽንና ባዛሮች አማካኝነት ሰዎች ለማዕድን ትኩረት መስጠት መጀመራቸውን ገልጻለች። አሁን አሁን ኢትዮጵያውያንም ጭምር ከከበሩ ድንጋዮች የሚሰሩ ጌጣጌጦችን ገዝተው መጠቀም መጀመራቸውን ተናግራለች።

ከከበሩ ድንጋዮች የሚዘጋጁት ጌጣጌጦች ለውጭ ገበያ ከማቅረብ ባለፈ የሀገር ውስጥ ሸማች በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት እንዲችሉ ታስቦ እንደሚሰሩም ገልጻለች። በተለይም የሀገር ውስጥ ሸማቾች በውጭ ሀገር ብልጭልጭ ሳይታለሉ በሀገራቸው ምርት እንዲኮሩና በሀገራቸው ውድና ብርቅ በሆኑ ማዕድናት ማጌጥና መዋብ እንዳለባቸው ነው ያመላከተችው።

ወጣት ኪያ እንዳለችው፤ ሀገሪቷ በማዕድን ሀብት እምቅ አቅም ያላት በመሆኑ መሰል ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቶችን ሰፋ ባለ መንገድ ማቅረብ ቢቻል ይበልጥ ምርቶችን መሸጥና ማስተዋወቅ ይቻላል። በተለይም የገበያ ትስስር የመፍጠርና ተመሳሳይ ምርት ከሚያመርቱ አምራቾች ደግሞ የዲዛይንና የተለያዩ የልምድ ልውውጦችን ማድረግ ይቻላል። ከዚህ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት በርካታ ጠቀሜታዎች እንደሚገኝ ጠቅሳ፣ ለዘርፉ ዕድገትም ወሳኝ መሆኑን ጠቁማለች።

የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት አምራቾች ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ጎሹ ነጋሽ  ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ ኢትዮጵያ ውስጥ መካሄድ ከጀመረ ስምንት ዓመታትን  ማስቆጠሩን ጠቅሰው፣ በየዓመቱ መሻሻሎች እየታዩበት መሆኑንና   ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉትም ተናግረዋል።

ሀገሪቱ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ዘርፍ እንዲሁም በፋሽን  ያለችበትን ደረጃ እና በዘርፉ ያላትን እምቅ አቅም ማሳየት እንደሚያስችል አስታውቀዋል። የሀገር ውስጥ አምራቾች ምርቶቻቸውን በማስተዋወቅ የገበያ ትስስር መፍጠር እንደሚያስችላቸው ተናግረው፣ ከግብዓት አቅራቢዎች ጋር በሚፈጥሩት ግንኙነትም የተለያዩ /የማጠናቀቂያ ግብዓቶችን/ አክሰሰሪዎችን የሚያገኙበትን አጋጣሚ እንደሚፈጥርም አመልክተዋል። ይህም አጠቃላይ በሀገሪቱ ያለውን የንግድ እንቅስቃሴ እንደሚያጠናክረውም ነው ያስታወቁት።

ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱም አፍሪካ ውስጥ አሉ ከሚባሉ አውደ ርዕዮች መካከል አንዱ እንደሆነ ፕሬዚዳንቱ አመላክተዋል። ከተለያዩ ሀገራት የሚመጡ ዜጎች  በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ እንደሚሳተፉ ጠቅሰው፣ በአብዛኛው ግን የአፍሪካ ሀገሮች እንደሚገኙበት ገልጸዋል።

ከ24 የተለያዩ ሀገራት የተውጣጡና ከ300 የሚበልጡ ላኪዎች ይሳተፉበታል። ዝግጅቱም የተለያዩ ምርቶችንና ፈጠራዎችን 6000 ለሚሆኑ የንግድና የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ አቅራቢ ባለሙያዎች እንዲሁም ለዓለም አቀፍ ታዳሚዎች የሚቀርቡበትና ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት ነው።

አውደ ርዕዩ ኢትዮጵያን የጨርቃ ጨርቅ መዳረሻ /ሃብ/ እናደርጋታለን የሚል ተልዕኮ ተይዞ  ከዓመታት በፊት መጀመሩን አስታውቀው፣ ዓለም አቀፍ ስጋት በነበረው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ አማካኝነት እንዲሁም ሀገሪቱ በገጠማት የሰላምና ጸጥታ ችግሮች በሚፈለገው ልክ መጓዝ እንዳልቻለ አመልክተዋል። እንዲያም ሆኖ ግን አሁን ላይ ጥሩ እንቅስቃሴ እንዳለም ፕሬዚዳንቱ ጠቅሰዋል።

አሁን ላይ በተዘጋጀው ላይ 20 የሚደርሱ ሀገር በቀል አምራቾች እንደሚሳተፉበት የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፣ ከኤዥያ፣ ከአውሮፓ፣ ከአሜሪካና ከአፍሪካ የመጡት ተሳታፊዎች ሀገሪቷ በጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት ያላትን አቅም ማየትና መረዳት የሚችሉበት ዕድል እንደሚፈጠር አመላክተዋል።

ፕሬዚዳንቱ እንዳሉት፤ በርካታ ያደጉ ሀገራት የኢኮኖሚ መሠረታቸውን በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ላይ አድርገው ነው ማደግ የቻሉት። በጨርቃ ጨርቅ ዘርፍ ካደጉ ሀገራት መካከልም እንደ ኮሪያ፣ ባንግላዲሽ፣ ቬትናምና ይገኙበታል። እነዚህ ሀገራት በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ዘርፍ በሀገራቸው ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛና መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት የቻሉ ሲሆን፣ ኢትዮጵያም ከእነዚህ ሀገራት ተሞክሮ በመውሰድ በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ዘርፉ ሙሉ አቅሟን አሟጣ በመጠቀም ውጤት ማምጣት ትችላለች። ለዚህም መሰል ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቶች ወሳኝ ናቸው።

በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ የሀገር ውስጥ አምራቾች ምርቶቻቸውን ሲያስተዋውቁና  ከውጭ የሚመጡት የተለያዩ ቴክኖሎጂና ግብዓት አቅራቢዎችም እንዲሁ ምርቶቻቸውን ሲያሳዩ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በብርቱ እንደሚነቃቃ ገልጸው፤ ለዚህም ማህበሩ የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ መሆኑን ፕሬዚዳንቱ አስታውቀዋል። በተለይም ተኪ ምርቶች ላይ በስፋት እየሰራ መሆኑን አመላክተዋል። ለአብነትም የመከላከያና የጸጥታ አካላት ዩኒፎርሞች በሀገር ውስጥ መመረት እንዲችሉ ማድረግ በራሱ አንድ ጅምር መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባ ተናግረዋል። ለዚህም ማህበሩ ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቱ መክፈቻ ላይ ተገኝተው የንግድ ትርዒቱን ያስጀመሩት የኢንዱስትሪ ሚኒስትር  አቶ መላኩ አለበል፤ መንግሥት በልማታዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች የኢትዮጵያን ብልፅግና እውን ለማድረግ እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

የመንግሥት የረጅም ጊዜ ራዕይ ኢትዮጵያን በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ በአፍሪካ ቀዳሚ ሀገር ማድረግና መካከለኛ ገቢ ያለው ማህበረሰብ መገንባት መሆኑን ጠቅሰው፤ ለዚህም የጨርቃ ጨርቅና ቆዳ ኢንዱስትሪዎች እሴት መጨመር፣ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት፣ የሥራ እድል መፍጠር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከል ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን አብራርተዋል። ኢትዮጵያን የጨርቃ ጨርቅና ፋሽን መናኸሪያ እንድትሆን ከሚያደርጉት ጉዳዮች መካከል የሀገር ውስጥ ገበያ፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተደራሽነት መሆናቸውንም  ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ እና በአኅራባች አፍሪካ ሀገራት ፋሽንን የሚያውቅ ሕዝብ ጥራት ያለው የአልባሳትና የጨርቃ ጨርቅ ፍላጎት እያደገ መምጣቱን ጠቅሰው፣ የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና እየሰፋ መምጣቱን ተከትሎ የኢትዮጵያ ምርቶች ፍላጎት የበለጠ እያደገ እንደሚሄድ አስታውቀዋል። በተለይም  በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ኢትዮጵያን የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ማምረቻ ማዕከል ለማድረግ በተጀመሩ ሥራዎች ትልቅ የኢንዱስትሪላይዜሽን ጉዞ መጀመር መቻሏን አመላክተዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ሰው የሚግባባው በምንድነው?

**ዋሰልኝ አየለ**

በደርግ ጊዜ ነው አሉ። አንድ የደርግ ካድሬ ወደ ገጠር ዘምቶ ገበሬውን ሰብስቦ ስለአብዮቱና መሰል ጉዳዮች የግንዛቤ ማስጨበጫ እየሰጠ ነው። በንግግሮቹ ውስጥ ‹‹ሌኒን እንዳለው፣ ስታሊን እንዳለው፣ ማርክስ እንዳለው....›› እያለ በወቅቱ ከደርግ ካድሬ አፍ የማይጠፉ አብዮተኞችን ይዘረዝራል። እነዚህ የተባሉት ሰዎች ምን እንደሆኑ የማያውቁት አንድ የገጠር አባት ተገርመው ‹‹እኔ እምለው? ይሄ አባ እንዳለው የሚባል ሰውዬ ስንት ልጆች ነው ያሉት?›› አሉ ይባላል። በገጠር አካባቢ እንዳለው የሚባል የሰው ስም ስላለ ካድሬው ‹‹እገሌ እንዳለው›› ሲል የተጠሩት ሰዎች አባታቸው እንዳለው ሆኖ ነው የመሰላቸው።

ከዚሁ ጋር የተገናኘ አንድ ቀልድ ልጨምር። ይህን ቀልድ የሰማሁት ከስድስት ዓመት በፊት ለመስክ ሥራ ከአዲስ አበባ ወደ ባህር ዳር እየተጓዝኩ ነበር። ደጀንን ይሁን ደብረ ማርቆስን እንዳለፍን አንድ ፖሊስ እንድንተባበረው ጠየቀን። መኪናችን ትርፍ ወንበሮች ስላሉት ገባ እና አብሮን መጓዝ ጀመረ። እንደሚታወቀው የመስክ ጉዞ ላይ ቀልዶች ይበዛሉ፣ ሳቅ ጨዋታ ይደምቃል። ብዙ ስንሳሳቅ ከቆየን በኋላ ፖሊሱን ‹‹እባክህ አንተም ተጫወት›› ዓይነት ጉትጎታ ተጀመረ። ‹‹ኧረ እኔ ምንም አላውቅም›› ቢልም እንደምንም ገፋፋነው። ምንም አላውቅም ብሎ የነገረን ቀልድ ግን እስከ ባህር ዳር ነበር ያሳቀን።

አንድ የመንግሥት የሥራ ኃላፊ እንደዚሁ ወደ ገጠሩ ማህበረሰብ ይላካል። የአካባቢውን ሕዝብ ሰብስቦ በል የተባለውን መልዕክት ያስተላልፋል። ሲናገር ታዲያ እንደተለመደው እሱም የወቅቱ መንግሥት ይጠቀማቸው የነበሩ የካድሬ ቃላትን ይደጋግማል። እነዚያን ቃላት ያልተረዱ ተሰብሳቢዎች ልቅም አድርገው በማውጣት ‹‹ይሄ ማለት ምን ማለት ነው? ይሄኛውስ ምን ማለት ነው?›› ይሉታል። እነዚያን ቃላት ማብራራት ያልቻለው ካድሬ ‹‹እኔ ምንም መቀየር አልችልም ከበላይ የመጣ ትዕዛዝ ነው›› አለ ብሎ የሰማውን ቀልድ ነገረን።

ቀልዶቹ በትክክል የተከሰቱ ሊሆንም ላይሆኑም ይችላሉ። የተፈጠሩ ቢሆኑ እንኳን ቀልዶቹ ለምን ተፈጠሩ ነው ዋናው ጥያቄ። ቀልዶቹ የተፈጠሩበት ምክንያት ከሚያጋጥመው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ነው። ብዙዎቻችን በተግባር እንደታዘብነው ለገጠሩ ማህበረሰብ የግንዛቤ ማስጨበጫ የሚሰጡ የመንግሥት ተወካዮች የአካባቢውን ዓውድ ባላገናዘበ መንገድ ነው። በመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች የሚዘወተሩ የፖለቲካ ቃላትን በመደጋገም ነው። መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚሄዱት አካላት ደግሞ የእንግሊዝኛ ቃላትን በመደጋገም ነው።

እዚህ ላይ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ እያለሁ በአካባቢያችን የሰማሁትን ምሳሌ ላድርግ። በወቅቱ (1990ዎቹ) ሰዎች ለሰዎች (ሜሽን ፎር ሜሽን) የሚባል ድርጅት በየአካባቢው የግንዛቤ ማስጨበጫ ይሰጥ ነበር። ታዲያ ይህን የሚያስተባብሩላቸው በየቀበሌው ያሉ ሚሊሻዎች ናቸው። አንደኛው ሚሊሻ ‹‹እዚህ ቦታ ላይ እንዲህ ዓይነት ነገር ስላለ›› በሚል ‹‹ኢንፎርሜሽን›› ተናገር ተብሏል። ሚሊሻው የትምህርት ዝግጅት ስለሌለው ለእንግሊዝኛ ቃላት በጣም ሩቅ ነው። በየመንደሩ እየዞረ ‹‹ፉርሽኝ አለ›› እያለ ነበር የሚናገር። የአካባቢው ሰዎችም ‹‹ፉርሽኝ ምን ይሆን?›› በማለት የሆነ የሚታደል ነገር በመጓጓት ነበር የሄዱት። እኔም በወቅቱ ‹‹ለምን መረጃ ብለው አይነግሩትም?›› እያልኩ ስናደድ ነበር።

ቀልዶቹም ሆኑ እውነተኛ ገጠመኞች ገጠር ላይ የሆኑበት ምክንያት የከተሜው ነዋሪ ለእንግሊዝኛ ቃላት ቀረብ ይላል በሚል ነው። የመገናኛ ብዙኃን ተደራሽነት ስላለው በተደጋጋሚ የመስማት ዕድሉ የተሻለ ይሆናል በሚል ነው። የገጠሩ ማህበረሰብ ግን የማንም የውጭ ድሪቶ የማያገኘው ቱባ የሆነ የራሱ ባህልና ቋንቋ ያለው ነው። በራሱ ቋንቋ መግባባት ብቻ ሳይሆን ቅኔ የሚቀኝ ነው። በራሱ ቋንቋ ጥልቅ መልዕክት ያላቸው ተረቶችና እንቆቅልሾች ያሉት ነው። ጥልቅ ፍልስፍና ያላቸው ወጎች ያሉት ነው።

ይህን ማህበረሰብ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚሄዱ ሰዎች ግን የአካባቢው ማህበረሰብ በሚገባው ቋንቋ አይደለም የሚያስረዱት፤ ራሳቸውም ባልገባቸው የውጭ ቃላት ነው። ሲባል የሰሙትን ቃል እዚያ ሄደው ይለማመዳሉ። እነዚያ የሚናገሯቸው የእንግሊዝኛ ቃላት ግልጽ የሆነ የአማርኛ አቻ ያላቸው ናቸው። ምንም እንኳን አንዳንድ የቴክኖሎጂ ቃላት ቢኖሩም ቢያንስ ግልጽ የሆነ ሀገርኛ ትርጉም ያላቸውን ቃላት ግን በአካባቢው ቋንቋ መናገር ትዝ አይላቸውም።

የሰው ልጅ ደመ ነፍሳዊ አይደለም። ከፍጥረታት ሁሉ ከሚለይባቸው ነገሮች አንዱ በቋንቋ የሚግባባ መሆኑ ነው። ቋንቋ መግባቢያ ነው። የሚያግባባ ቋንቋ ደግሞ የጋራ ቋንቋ ይባላል። ለምሳሌ፤ ይህን ጽሑፍ የጻፍኩት በአማርኛ ቋንቋ ነው። ይህን ጽሑፍ የሚያነበው አማርኛ ማንበብ የሚችል ሰው ነው። ስለዚህ ይህ ቋንቋ የእኔ የፀሐፊው እና የዚህ ጽሑፍ አንባቢ ሰው የጋራ ቋንቋ ነው ማለት ነው። ተግባባን ማለት ነው። ምንም አማርኛ የማይችል አንድ ቻይናዊ ይህን ጽሑፍ ቢያየው ሊያነበው አይችልም፤ ስለዚህ ለዚህ ሰውዬ የጋራችን አልሆነም ማለት ነው። ይሄ ሰውዬ እኔን ግንዛቤ ሊያስጨብጠኝ ወይም እኔ ላስጨብጠው አንችልም ማለት ነው። እኔና እርሱ ልንግባባ የምንችለው የጋራ ሊሆን በሚችለው በእንግሊዝኛ ይሆናል ማለት ነው።

እነዚህ ግንዛቤ ሊያስጨብጡ የሚሄዱ ሰዎች የመረጡት ቋንቋ አማርኛ ነው እንበል። ሊያስተምሩ የሚሄዱትም የአማርኛ ተናጋሪ ባለበት አካባቢ ነው። የሚገርመው ሊያስተምር የሚሄደውም የአፍ መፍቻ ቋንቋው አማርኛ ሊሆን ይችላል፤ ምናልባት እንደማንኛውም ሰው በትምህርት ያገኛት የእንግሊዝኛ ዕውቀት ትኖራለች።

አንድን ሃሳብ በሰዎች ላይ ለማስረጽ በሚገባቸው ቋንቋ መሆን አለበት፤ እንዲያውም እንኳን ቋንቋው አቀራረቡ ራሱ ሳቢ መሆን አለበት ነው የሚባለው። እየሆነ ያለው ግን ጭራሽ ቃላቱ ራሱ የሚናገረው ሰው የማያውቃቸው ናቸው። መሆን የነበረበት ግን ቋንቋውን እነርሱ የሚያውቁት ማድረግ ብቻ ሳይሆን አቀራረቡ ራሱ በእነርሱ ዓውድ ነው። ምሳሌ ሲሰጥ በአካባቢያቸው የሚያውቁት ነገር መሆን አለበት። የሚነገሩት ቃላት አማርኛ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን የአካባቢው ሕዝብ የሚያውቀው አማርኛ ነው ወይ የሚለው ታሳቢ መደረግ አለበት።

በገጠር አካባቢ የሚሰማሩ የግብርና ባለሙያዎች፣ የጤና ባለሙያዎች እና በተለያዩ ወቅታዊና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚላኩ ባለሙያዎች መጀመሪያ ራሳቸው መሰልጠን አለባቸው። አወዛጋቢና አሻሚ ትርጉም ያለው ያልተለመደ ቃል ባይጠቀሙ፤ ሲጠየቁ ሊያብራሩት የሚችሉትን ቃላት ነው መናገር ያለባቸው።

ቃላት መረጣ ብቻ ሳይሆን አቀራረብ ራሱ በተቻለ መጠን ለአካባቢው ሕዝብ ቢሆን ዓውድ ቢሆን። ከባለሥልጣናት እና ከምሁራን ጋር እንደሚደረገው ውይይት መደበኛ እና ፕሮቶኮሉን የጠበቀ ከሚሆን ይልቅ እንደ ደንባቸው ኢመደበኛ እና ቀለል ያለ ቢሆን። ምክንያቱም ነፃ ሆነው ሃሳባቸውን ሊናገሩ ይችላሉ። ይህ እንኳን ባይቻል፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሲሰጥ ትምህርቱ የሚሰጣቸው ሰዎች በሚገባቸው አገላለጽ ይሁን!

# ዓለም አቀፍ

## ለወታደሮች የተጻፉት ደብዳቤዎች ከ265 ዓመታት በኋላ የመነበብ ዕድል አገኙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በብሪታንያ እና በፈረንሳይ መካከል በተደረገው የሰባት ዓመታቱ ጦርነት የተጻፉ ደብዳቤዎች ከ265 ዓመታት በኋላ የመነበብ ዕድል አግኝተዋል።

እንደአሁኑ ማሕበራዊ ሚዲያ ተደራሽ ባልሆነበት ዘመን ሰዎች ሰላምታቸውን፣ ፍቅራቸውን፣ ናፍቆታቸውንና ፍላጎታቸውን በወረቀት አስፍረው ለልባቸው ሰው እንዲደርስ በመልእክተኛ ይልካሉ፡፡

መልዕክተኛው በቶሎ ካደረሰው እሰየው ብለው ምላሽን ይጠባበቃሉ ፤ ካላደረሰው ደግሞ የዚያኑ ያህል እረፍት ይነሳል፡፡

መልዕክታቸው የደረሰ እንደሆነም ምላሽ መጠበቁ በራሱ የዘላለም እድሜን ያክልባቸዋል፤ ከወደዱት ሰው መራቅ፣ የወደዱትን እንደልብ አለማግኘት፣ የተሰማን የፍቅርና የናፍቆትን ስሜት በአንድ ደብዳቤ አጭቆ መጻፍን ይፈትናል፡፡




በዚህ መልኩ ተጽፈው በጊዜው ለተላከላቸው ፈረንሳውያን ወታደሮች ሳይደርሱ የቀሩ 104 ደብዳቤዎች ከሰሞኑ ከ265 ዓመታት በኋላ ተከፍተው ተነበዋል።

ደብዳቤዎቹ በአብዛኛው ለታሰሩ የፈረንሳይ መርከበኞች የተላኩ እንደነበሩ ቢዝነስ ኢንሳይደር እና ቢቢሲ አስነብበዋል።

ደብዳቤዎች በወቅቱ በብሪታንያ እና በፈረንሳይ መካከል በተደረገው የሰባት ዓመታቱ ጦርነት እ.አ.አ. በ1757/58 ለፈረንሳውያን መርከበኞችና ወታደሮች የተጻፉ እንደነበሩ የካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ተመራማሪ የሆኑት ፕሮፌሰር ሬናድ ሞሪዩ ይገልጻሉ።

ደብዳቤዎቹ በብሪታንያ ኬው ለንደን በሚገኘው ብሔራዊ ቤተመዛግብት ውስጥ ለታሰበው ሰው ሳይደርሱና ሳይነበቡ የቆዩ ሲሆን በመጨረሻም በታሪክ ተመራማሪው ተከፍተው ተነበዋል።

በወቅቱ ወታደራዊ ይዘት ሊኖራቸው ይችላል በሚል በእንግሊዝ ወታደሮች ተይዘው ቢቀመጡም ናፍቆትን ያዘሉ በርካታ ደብዳቤዎች እንደነበሩ ተመራማሪው ተናግረዋል።

ከዚህ ውስጥ አን ለ ሰርፍ የተባለችው እመቤት ለባለቤቷ የጻፈችው የናፍቆት ደብዳቤ ይገኝበታል።

ደብዳቤው ‘በልቤ ውስጥ ላለኸው ግን ላገኝህ ያልቻልኩት ውዱ ባለቤቴ’ በሚል ይዘት የተጻፈና የቆየ ናፍቆትና ፍቅሯን የገለጸችበት ነው።

“ውዱ ባለቤቴ ላንተ እየጻፍኩ ሌሊቱን ላነጋው እችላለሁ ...እኔ ታማኟ ሚስትህ ማሪ ዱቦስክ ነኝ...” በሚል የተጻፈውና ለመጀመሪያዋ የፈረንሳይ የጦር መርከብ አዛዥ ያልደረሰው ደብዳቤም ከ265 ዓመታት በኋላ በታሪክ ተመራማሪው የተከፈተ ደብዳቤ ነው።

ይህ ደብዳቤ የተጻፈለት የጦር መርከብ አዛዥ ደብዳቤውም ሳይደርሰውና ከባለቤቱ ጋር ዳግም ሳይገናኝ ከአንድ ዓመት ቆይታ በኋላ በሰሜናዊ ፈረንሳይ በጦርነቱ ሕይወቱ አልፏል ነው የተባለው።

”ከአጠገቤ አለመኖርህን ልቋቋመው አልቻልኩም፤ ቀናት ወራትን ወራት ደግሞ ዓመታትን እየወለዱ ... ” እና መሰል ይዘት ያላቸው ደብዳቤዎች ለተላኩለት ሰው ሳይደርሱ ከ265 ዓመታት በላይ አስቆጥረዋል፡፡

እነዚህ ደብዳቤዎች ለፈረንሳይ እስረኞች የተላኩ የፍቅርና የናፍቆት ደብዳቤዎች ናቸው፤ ሆኖም ደብዳቤዎቹ የያዙትና ሚስት ለባለቤቷ ቤተሰብ ለልጆቹ የላኳቸው ፍቅርና ናፍቆት ሳይነበቡና ምላሽ ሳያገኙ እስከወዲያኛው አልፈዋል፡፡

እ.አ.አ. ከ1756 እስከ 1763 በፈረንሣይ እና በብሪታኒያ መካከል የተደረገው ጦርነት በአሜሪካ መሬት ይገባኛል ምክንያት የተካሄደ ነበር።

በዚህ ጦርነት ወደ 20 ሺህ የሚጠጉ ፈረንሳውያን መርከበኞች በብሪታንያ ጦር ተይዘው የነበረ ሲሆን፥ ለእነዚህ እስረኞች ከፍቅር አጋሮቻቸውና ቤተሰቦቻቸው የተላኩ ደብዳቤዎች ሳይደርሳቸው ወደእንግሊዝ ተመልሰው እንደተላኩም ነው የተነገረው፡፡

በወቅቱ ሁለት ደብዳቤዎችን ከፍተው ያዩት በጊዜው የነበሩት የእንግሊዝ ባለስልጣናት ደብዳቤዎቹ ሌላ ዓላማ እንደሌላቸው ከተገነዘቡ በኋላ እንኳን ለተላኩላቸው ሰዎች መስጠትን አልፈለጉም ነበር፡፡

ደብዳቤዎቹን ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍተው ያነበቧቸው ፕሮፌሰር ሬናድ፥ “የተጻፉላቸው ሰዎች ይህን እድል አላገኙም፤ ይሄ እጅግ ስሜታዊ ያደርጋል” በማለት የተሰማቸውን ገልጸዋል።

“እንደ ወረርሽኝ ወይም ጦርነት ከአቅማችን በላይ በሆኑ ክስተቶች ከምንወዳቸው ሰዎች በምንለይበት ጊዜ እንዴት መገናኘት እንዳለብን፣ እንዴት ማረጋጋት እንደምንችል፣ ሰዎችን እንዴት እንደምንከባከብ ማወቅና ስሜቱን መጠበቅ ይገባልም” ነው ያሉት።

የሰባት ዓመታቱ ጦርነት እ.አ.አ ከ1756–1763 ድረስ ብሪታንያ እና በፈረንሳይ መካከል የተካሄደ ጦርነት ነው። በወቅቱ በፈረንሳይ እና በእንግሊዝ መርከቦች መካከል የባህር ኃይል ጦርነት ከተደረገ በኋላ በተለያዩ ስፍራዎች ላይ ደም አፋሳሽ ውጊያዎችን አድርገዋል።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## የ15 ዓመት ጥያቄ ለ25 ዓመታት በረከት

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

በርካታ ዓመታትን በጎዳና ላይ አሳልፏል፤ ብርድና ሀሩሩ፤ ተባይና ነፍሳቱ ሲያሰቃዩትም ከርሟል። በሽታው ደግሞ ከዚህም ይለያል። ለወራት ያህል የአልጋ ቁራኛም ሆኖ ሰንብቷል። አንዳንዱ ስቃዩ አሳዝኗቸው ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ ተጸይፈውት ነጋ ጠባ ሰዎች ሞቱን ሲሹለትም ነበር። በዚህ ስቃይ ውስጥ የነበረው ይህ ብርቱ ሰውም አንድ ቀን አምላኩን አንድ ነገር ለመነ። ይህቺም ዕለት ደግሞ በጠና የታመመባት ነበረች።

‹‹አምላኬ ሆይ ሙሉ አካል ኖሮኝ ፤ ሙሉ ጤና ሰጥተኸኝ የተቸገሩትን አይቼ አላልፍም። ስለዚህም እኔ ስቸገር ሰዎች ሊደርሱልኝ አልቻሉም። እናም ደራሼ አንተ ብቻ ነህና ጤናዬን መልስልኝ። የ15 ዓመት እድሜን ብቻ ጨምርልኝ። በዚህች የእድሜ ጭማሬ ላይም ወገኔን ላገልግል›› ሲልም ነበር የወደቁትን አንሱ የነደያን መርጃ ማህበር መስራች አቶ ስንታየሁ አበጀ ልመናውን በእንባ ጭምር ወደ አምላኩ ያቀረበው።

አቶ ስንታየሁ ጤናው ሲመለስለት ነገ የገባሁትን ቃል አከብራለሁ፤ ዛሬ ራሴን ልለውጥ አላለም። ልክ ገና ከሕመሙ እንዳገገመ ነው ቃሉን በተግባር ለመለወጥ ሥራውን አሀዱ ያለው። ትናንት እርሱ የነበረበትን ሕይወት ሌሎች እንዳይኖሩት ለማድረግ ከሚኖርበት አካባቢ ነበርም ሥራውን የጀመረው። የሚኖርበት አካባቢ አዲስ አበባ ጉለሌ ክፍለ ከተማ በተለምዶ ሽሮ ሜዳ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ሲሆን፤ ሰዎችን ከወደቁበት አንስቶ አጥቦና አልብሶ በተቻለው ሁሉ መመገብ ነበር። ሰዎችን የሚሰበስብበት ቦታ ግን አልነበረውም። እናም አረጋዊያንን ቢያነሳቸውም የሚያስቀምጥበት ቦታ የት መሆን እንዳለበት ያውጠነጥን ጀመር።

በመጨረሻም አንድ ሃሳብ ላይ ውሳኔውን አሳረፈ። በአቅራቢያው የኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አለችና የመቃብር ባለቤቶችን ቤት በማስፈቀድ አረጋውያኑን፣ ሕሙማኑን፣ አካል ጉዳተኛውን ለማሰባሰብ አሰበ። አስቦም ብቻ አልቀረም ፤ ፈቃዱን አገኘና ወደ ተግባሩ ገባ።

የአቶ ስንታየሁ ጥንካሬና ቃል አክባሪነት የሚታየው ማህበሩን ሲጀምረው የነበረው ሁኔታ ነው። ለሦስት ወር የአልጋ ቁራኛ ከመሆኑ በፊት ያጠራቀማትን ስምንት ሺህ ብር ይዞ ሥራውን ለመጀመር ነበር ሃሳቡ። ሆኖም ያጠራቀመው ብር ጥቅም ላይ የሚውል አልሆነለትም። ምክያቱም ታማሚ ስለነበር የብር ማስቀመጫው ፍራሹ ሥር ስለነበር በሥርዓት ባለመቀመጡ የተነሳ ከጥቅም ውጭ ሆኗል፤ ሻግቶም አገልግሎት የሚሰጥ አልነበረም። ከዚህ ውስጥ ደህና ሆና የተገኘችው ሁለት ብር ብቻ ናት። ሁለት ብር ምንም ማድረግ አይችልም።

ለትናንቱ እድሜ ለማኝ ለዛሬው ቃል ተርጓሚ ሰው ግን ሁለት ብር ዋጋ ነበራት። የውኃ መቅጃ ጀሪካን ተገዝቶባት ለብዙ አቅመ ደካሞች ንጽህና መጠበቂያ ውኃን ማመላለሻ ሆናለች። ብዙዎችን ከውሃ ጥምና ከርሃብ መታደግ እንዲቻልባት እድል ሰጥታለች። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ዓመታት ቢገፉም ዘለቄታዊነቱ ግን በብዙ መልኩ እንዲፈተን ሆኗል። አንደኛው የማኅበሩ ሕጋዊ ዕውቅና ጉዳይ ሲሆን፤ ይህንን ከብዙ ድካምና ልፋት በኋላ በ1990 ዓ.ም. አሳክቶታል።

‹‹ከሕመሜ ከተፈወስኩኝ ጧሪ ቀባሪ ያጡትን አረጋውያን፣ ሕሙማንና አካል ጉዳተኞችን በቀሪው የሕይወት ዘመኔ አገለግላለሁ›› የሚለው ቃሉም እስከዛሬዋ ዕለት በመፈጸም ላይ የሚገኘው ስንታየሁ፤ ሁሌም ተስፈኛ ነው። ትናንት ማህበሩን ሲመሰረት እንኳን ብዙ ካፒታል ሳይኖረው ማህበረሰቡን አጋሮቹ እንደሚሆኑ አምኖ ዛሬን አይቷል። ነገም ቢሆን በዚህ መልኩ እንደሚቀጥል ያስባል። ምክንያቱም እርሱ 15 ዓመት ቢጠይቅም 25 ዓመታትን ተችሮት የማህበሩን የኢዮቤልዮ ዓመት እንዲያከብር አድርጎታል። በዚህ ውስጥ ደግሞ ብዙ ነገሮችን መለወጥ ችሏል።

ለአብነት ትናንት በሁለት ብር በገዛት ጀሪካን ውኃ በአካባቢው ካለ ወንዝ በማመላለስ የአረጋዊያኑን



ገላ፣ ልብሳቸውን ያጥብ ነበር። የሚውሉበትን የሚያድሩበትን ቤት ያጸዳልም፤ ከሕዝብ የተሰበሰበውን ምግብ በማቅረብና በመመገብ ቃሉን በተግባር ይተረጉምም ነበር። ዛሬ ደግሞ ነገሮች ተቀይሮ ጀሪካኑ ከቧንቧ እንጂ ርቀት ሄዶ ከወንዝ አይቀዳበትም። ሕዝቡም ቢሆን በተሰራለት ንጹህና ባለፎቅ ቤት ብቅ እያለ ይመግበዋል፤ አይዞህ እያለም ያለብሰዋል። በተጨማሪም እንክብካቤ የሚያደርጉ ሠራተኞችና የጤና ባለሙያዎች ሞልተዋል።

አረጋውያን ከኅብረተሰቡም ሆነ ከሚመለከተው አካል ተገቢው ትኩረት እየተሰጣቸውም ነው። ለዚህ ደግሞ የማኅበራቸው መመስረት ዋነኛ መሠረት ነው። በአሁኑ ጊዜ ማዕከል አስገንብቶ ከ200 በላይ የሚሆኑ አረጋውያንን እየተንከባከበ ይገኛል። በተጨማሪም ከማዕከሉ ውጭ ሆነው በተመላላሽ አገልግሎት የሚያገኙም እንዳሉ ጠቁሟል። በተጨማሪም የወደቁትን አንሱ የነዳያን ማኅበር አረጋውያንን የሚንከባከቡ ነርሶችንም የአጭር ጊዜ ልዩ ሥልጠና በመስጠት የሕክምና ዕርዳታን እየሰጡ ነውም።

ይህ ሁሉ ለውጥ ደግሞ የተነሳው ከሰሞኑ በተከበረው የአረጋውያን ቀን ላይ ሲሆን፤ ማህበሩም ጎን ለጎን በተለያዩ መርሐ ግብሮች 25ኛ ዓመቱን አክብሯል። እናም አቶ ስንታየው በክብረ በዓሉ ላይ እንዳለው፤ ማህበሩ ዘርፈ ብዙ ሥራ በአረጋውያኑ በኩል ይሠራል። አንደኛውና ዋነኛው አረጋውያኑን መንከባከብ ሲሆን፤ ሌላኛው ተግባሩ ደግሞ ሕይወታቸው ያለፉ ሰዎችን ለማዘጋጃ ቤት በማሳወቅ ሰዎቹ በክብር እንዲቀበሩ ማድረግ ነው። በተጨማሪም እንደየእምነታቸው ተለይተው እንዲቀበሩም ያመቻቻል።

አቶ ስንታየሁ ሥራውን ጀምሮ በብዙ ፈተና ውስጥ እያለ ሁለት ወጣቶችን ተዋውቋል። ንጉሤ ሀብታሙና ካሳሁን ከበደ የሚባሉ ወጣቶች ናቸው። ሥራው ተመልክተው እርሱን ለማገዝ የታተሩ ሲሆኑ፤ ተሳትፏቸው ደግሞ ራሳቸውን ብቻ የያዘ አልነበረም። ቤተሰቦቻቸውን ጭምር አሳትፈውና አስተባብረው ከማኅበሩ ምሥረታ ጀምሮ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ የቆዩ ናቸው። ዛሬም ቢሆን ከስንታየሁ ጎን ቆመው የቻሉትን ሁሉ እያደረጉ ይገኛሉ። አቶ ሰንታየሁ ስለእነርሱ ሲያወሳ ‹‹አምላክ ለሰዎች በሰዎች ላይ አድሮ ይደርሳልና የእኔን ቃል እንድተገበር እነርሱን ጨመረልኝ›› ይላል።

አቶ ስንታየሁ ዘወትር ከአፉ የማይለየው አንድ አባባል አለው። ይህም ‹‹ልጅ አይሙት ይታመም›› የሚለው ሲሆን፤ ምክንያቱ ደግሞ ልዩ ልዩ ነው። አንደኛው በልጅ ሕመም ውስጥ መሥራትና ለሌሎች መኖርን ማየት ይቻላል። በሕመም ውስጥ የሌሎችን ችግር መጋራትና ለመፍትሔ መነሳትን ያመጣል። እናም እርሱ ልጅ ነበረ፤ በሕመሙ ውስጥ ዓመታትን ተሻግሮ ሌሎችን አየ፤ ለማስታወስም ቻለ። እናም ሌሎችም ይህንን ያደርጋሉ ብሎ ያምናል።

ማህበሩ 25ኛ ዓመቱን ሲያከብር ብዙዎችን ያሰባሰበ ሲሆን፤ በወቅቱ የተገኙ የተለያዩ ተጋባዥ እንግዶች መካከል የአርበኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ አንዱ ናቸው። በፎቶ አውደ ርዕዩ መክፈቻ ወቅት እንደተናገሩትም፤ ‹‹አረጋዊያን ሀገርን በደማቸው ያሻገሩ፤ ትውልድን በምርቃት የገነቡ ችግር መፍቻ ቁልፎች ናቸው። ነገ ምን እንደሚሆን ቀድመው የሚተነብዩና የሚያዩ ፤ ለሌሎች ጭምር የሚያመላክቱ ነብያቶችም ናቸው። በዚህ ውስጥ ግን የሚመለከታቸው ያጡና ምርቃታቸውን ሳይሆን ርግማናቸውን እየሰጡ ያለፉ ሆነዋል። እናም አሁን ተረጋሚ እንዳንሆን ሳይወድቁ ልናነሳቸውና ልንንከባከባቸው ይገባል። የዚህን ጊዜ ከምርቃታቸው በረከትን፤ ከተሞክሯቸው ነጋችንን እናገኛለን።›› ብለዋል።

ሌላው በክብረ በዓሉ ላይ የተገኙትና ንግግር ያደረጉት ደግሞ በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ የሚኒስትሯ አማካሪ አቶ ሰለሞን አስፋው ሲሆኑ፤ ማህበሩ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ በቁጥር 1195 ህጋዊ የምዝገባ ፍቃድ አግኝቶ እየሰራ የሚገኝ መሆኑን ለታዳሚው አስረድተዋል። ቀጥለውም እንዳሉት፤ በርከት ያሉ መደበኛ አባላቶችና በጎ ፍቃደኛ አባላቶች ያሉት ሲሆን፤ ሃይማኖት፣ ዘርና ፆታ ሳይለይ የሦስተኛ ወገን ድጋፍ ለሚያስፈልገው ሰው ለሆነው ፍጡር ሁሉ አገልግሎት የሚሰጥ ግብረ ሰናይ ድርጅት ነው ሲሉ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ የማህበሩ የሀብት ምንጭ በዋነኛነት ዓላማው አድርጎ የተነሳው እኛው በእኛው በሚል መርህ ከኢትዮጵያዊ ግለሰቦች፤ በኢትዮጵያ ህጋዊ ሰውነት አግኝተው ከሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች፤ ተገልጋዮችን በየጊዜው ከሚጎበኙ ግለሰቦችና ድርጅቶች በዓይነትና በገንዘብ ከሚያገኘው ድጋፍ በየወሩ ከመደበኛ አባላት ከሚሰበሰብ መዋጮ ነው። የሰው ኃይልን በተመለከተ በባለሙያ በጎ ፍቃደኞች የሚደረግ የሙያ እገዛን ያካተተ ነውም።

አቶ ሰለሞን፤ ማህበሩ በአሁኑ ሰዓት ከ200 በላይ ለሚሆኑ አረጋውያኖች ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ በምግብ፣ በአልባሳት፣ በመጠለያ፣ በሕክምና እንዲሁም ክብርና ፍቅር በመስጠት አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን አንስተው፤ ከወረዳው ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት፣ ከወረዳው አረጋውያን ማህበር እንዲሁም ከአካባቢው እድሮች በሚያገኘው መረጃ መሠረት ደጋፊ ወገን የሌላቸውን አረጋውያን በመለየት በማዕከሉ ቅጥር ግቢ መጥተው በየዕለቱ የምግብ አገልግሎትና በመካከለኛ ክሊኒኩ የነጻ ሕክምና በመስጠት ቁጥራቸው ከ100 ለማያንሱ ችግረኛ አረጋውያን ድጋፍ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ይጠቅሳሉ። በተጨማሪም በዓልን አስመልክቶ የምግብ፣ የንጽህና እቃና አልባሳት ድጋፍ እንደሚያደርግም ነው የሚያብራሩት።

ማህበሩ በቀጣይ የአገልግሎት አድማሱን በማስፋት ትልቅ ርዕይ መሰነቁንና በ2040 በአረጋውያን ሁለንተናዊ ድጋፍ፣ እንክብካቤና ሕክምና በምስራቅ አፍሪካ ቀዳሚ ሆኖ መገኘት ነው በሚል ጉዞውን ለመጀመር በመንደርደር ላይ መሆኑን የጠቆሙት አማካሪው፤ በዚህም መሠረት በሀገራችን የመጀመሪያ የሚሆነውን የአረጋውያን ሕክምና ማዕከል ለመገንባትና አገልግሎት ለመስጠት የዲዛይንና የእስታንዳርድ ጥናት እያስጠና እንደሚገኝ ተናግረዋል። ይህ ደግሞ ለአረጋውያኖች ከሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት በተጨማሪ ማዕከሉ በጥናትና ምርምር እንዲሁም ለሕክምና ባለሙያዎች ስልጠና የሚሰጥበት የልህቀት ማዕከል እንደሚሆን አብራርተዋል።

ማህበሩ አሁን ባለበት ሁኔታ ለዚህ ሕክምና የሚሆን የባለሙያ ፍላጎት ለማሟላት የአረጋውያን ነርሶችን የማስልጠን ሂደት መጀመሩንና የማኅበሩ ፖሊሲና ስትራቴጂ የሀገር ውስጥ ሀብትና እውቀትን በማስተባበር ኢትዮጵያዊነትን የተላበሰ አስተሳሰብ ይዟል ይላሉ። ‹‹በህብረተሰብ የሚደገፍ ወገን ለወገኑ መደጋገፍ ይችላል›› በሚል መርህ የወገን ተደራሽነቱን በተግባር ያሳየ እና ለሌሎች መሰል ድርጅቶች አርአያ የሚሆን እንደሆነም ያነሳሉ። በተጨማሪም በአረጋውያን ዙሪያ ከሚሰሩ መሰል ድርጅቶች ጋር ትስስር ፈጥሮ እየሰራ መሆኑ የአረጋውያኖችን ድምጽ በጋራ በማሰማት፤ የልምድ ፡ ለውውጥ በማድረግና በአጠቃላይ እርስ በእርስ በመረዳዳት ጥሩ ውጤት እያስመዘገበ እንዲሄድ አድርጎታልም ባይ ናቸው። እናም ዛሬም ሆነ በቀጣይ ይህንንና መሰል ድርጊቶቹን በመደገፍ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ከጎኑ እንደሚሆን አረጋግጠዋል።

አዎ እንደ እነዚህ ዓይነት ተግባራት በመንግሥት ብቻ ሳይሆን ከመንግሥት ውጭ ባሉ ሌሎች ድርጅቶችም ሊደገፉ ይገባል። ምክንያቱም ጉዳዩ ሰውን ማገዝ ነው፤ ሰውን ከአለበት ችግር መታደግና ለነገ የሚሆን መልካም ስንቅ ማስቀመጥ። አቶ ስንታየሁ መልካሙን ነገር ተመኝቶ 15 ዓመት ጠይቆ 25 የበረከት እድሜ እንደተሰጠው ሁሉ በዚህ መልካም ሃሳብ ውስጥ ሁሉ የተሳተፈ ሰው የበረከት እድሜን ያፍሳል። ስለዚህም ተግባሩ መልካምነትን መቃረሚያ ነውና ሁሉም ይጠቀምበት እያልን ለዛሬ የያዝነው በዚህ አበቃን። ሰላም!!

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ
ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency



ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የሴቶች ፕሪሚየር ሊግና ከፍተኛ ሊግ ጨዋታዎች የሚጀመሩበት ቀን ታውቋል

ዓለማየሁ ግዛው

የ2016 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሴቶች ፕሪሚየር ሊግና ከፍተኛ ሊግ ውድድሮች የሚጀመሩበትን ቀንና ቦታን የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ከትናንት በስቲያ ባካሄደው የዕጣ ማውጣት ሥነ ሥርዓት ይፋ አድርጓል። የኢትዮጵያ ሴቶች ፕሪሚየር ሊግ በሐዋሳ ከተማ የሚካሄድ ሲሆን የሴቶች ከፍተኛ ሊግ ውድድር በባቱ ከተማ እንደሚካሄድ ተገልጿል።

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የሚመራቸው የእነዚህ ውድድሮች የመጀመሪያ ሳምንት ጨዋታዎች የዕጣ ማውጣት ሥነ ሥርዓት ጥቅምት 26- 2016 ዓ.ም ተደርጓል። የዕጣ ማውጣት ሂደቱን የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ ጅራ፣ የውድድር ዳይሬክቶሬት፣ የሴቶች ልማትና ውድድር ኮሚቴ አባላት እና የሴቶች ፕሪሚየር ሊግና ከፍተኛ ሊግ ክለብ ተወካዮች በተገኙበት ተካሂዷል። የ2015 ዓ.ም የውድድር ሪፖርቶች እና የ2016 ዓ.ም የውድድር ደንብ ቀርቦም ውይይት ከተደረገበት በኋላ ፀድቋል። በመድረኩም ለሴቶች እግር ኳስ ትኩረት በመስጠት መሠራት እንደሚኖርበትና በክለብ ፈቃድ አሰጣጥ እና የፊዚዮቴራፒስት የሕክምና ጉዳይ ላይ ሰፊ ሥራ ለመሥራት ጥረት እንደሚደረግ ተጠቁሟል።

በወጣው መርሐግብር መሠረት የዘንድሮ የኢትዮጵያ ሴቶች ፕሪሚየር ሊግ ከኅዳር 16 -2016 ዓ.ም ጀምሮ በሐዋሳ ከተማ እንደሚከናወን ተገልጿል። 14 ክለቦችን የሚያፎካክረው የሴቶች ፕሪሚየር ሊግ በመጀመሪያ ሳምንት የሚደረጉት ጨዋታዎችም ይፋ ተደርገዋል። የአምናው የሊጉ ቻምፒዮን ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከሐዋሳ ከተማ ጋር ጨዋታውን በማድረግ የውድድር ዓመቱን የሚጀመር ሲሆን በሌሎች የሊጉ የመጀመሪያ ሳምንት ጨዋታዎች ቦሌ ክፍለ ከተማ ከመቻል፣ ልደታ ክፍለ ከተማ ከአርባምንጭ ከተማ፣ ድሬዳዋ ከተማ ከአዳማ ከተማ፣ ይርጋጨፌ ቡና ከቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ሀምበርቾ ከኢትዮ ኤሌክትሪክ እና አዲስ አበባ ከተማ ከሲዳማ ቡና በሚያደርጓቸው ጨዋታዎች ሊጉ ጅማሬውን የሚያደርግ ይሆናል።



የ2016 ዓ.ም የሴቶች ፕሪሚየር ሊግና ከፍተኛ ሊግ ውድድሮች ከቀጣይ ወር አጋማሽ ጀምሮ ይካሄዳሉ፣

የሴቶች የከፍተኛ ሊግ ውድድር ደግሞ ከኅዳር 22 ጀምሮ በባቱ ከተማ እንደሚደረግ የፌዴሬሽኑ አመራሮች፣ የክለብ ተወካዮች እና ጥሪ የተደረገላቸው አካላት በተገኙበት በተደረገው የዕጣ ማውጣት መርሐ-ግብር ወቅት ተገልጿል። በዚህም በመጀመሪያ ሳምንት ጨዋታዎች 11 የከፍተኛ ሊግ ክለቦች በመኖራቸው በመጀመሪያ ሳምንት 6 ጨዋታዎች ሲካሄዱ አንድ ክለብ ጨዋታን የማያደርግ ይሆናል። በወጣው መርሐ ግብር መሠረትም ንፋስ ስልክ ላፍቶ ከጉለሌ ክፍለ ከተማ፣ አቃቂ ቃሊቲ ከቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ ሸገር ከተማ ከለሚ ኩራ፣ ባህርዳር ከተማ ከአምቦ ጎል (ፊፋ) እና ሞጆ ከተማ ከፋሲል ከነማ በመጀመሪያ ሳምንት ጨዋታቸውን የሚያካሂዱ ሲሆን የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ የሚያርፍ ቡድን ይሆናል።

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ ጅራ በመርሐ ግብሩ ላይ ባደረጉት ንግግር፣ በቀጣይ ለሴቶች እግር ኳስ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት እንደሚኖርበት ገልጸዋል። የተፎካካሪ ክለቦች ቁጥር ቢጨምር በብሔራዊ ቡድን ደረጃ ኢትዮጵያ ውጤታማ መሆን እንደምትችልም ተናግረዋል። ለዚህም ክለቦች ትኩረት ሰጥተው በመሥራትና የተፎካካሪ ክለቦችን ቁጥር በመጨመር የሴቶችን እግር ኳስ አንድ እርምጃ ወደ ፊት በማምጣት የፌዴሬሽኑን ጥረት መደገፍ እንደሚኖርባቸው አሳስበዋል። ፌዴሬሽኑ የወንድ ክለብ ያላቸውን ክለቦች ተከታትሎ የሴት ክለብ እንዲመሰርቱ የማድረግ ክፍተቱን በማስተካከል ሁሉም ክለቦች የሴቶች እግር ኳስ ክለብ እንዲያቋቁሙ እንደሚሰራም ጠቁመዋል።

ለዚህም የክለብ ፍቃድ አሰጣጥና ምዝገባ ከ15 ዓመት በፊት በዓለም አቀፉ የእግር ኳስ ማኅበር ፊፋ ሥልጠና የተሰጠ ቢሆንም የተሻሻለ ነገር አለመኖሩን ገልጸዋል። በመሆኑም ፌዴሬሽኑ አዲስ ባለሙያ ቀጥሮ ግብጽና ታንዛኒያ በመላክ ሥልጠና እንደሰጠና የኢትዮጵያ ክለቦች ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያን በማዘጋጀት ለክለቦች የግንዛቤ ሥልጠና ከተሰጠ በኋላ መነቃቃት ተፈጥሯል። የክለብ ፍቃድ ሕጉ የሚለውን፣ መሬት ላይ ያለውን እና መጨመር ያለበትን ዓለም አቀፉን የሴቶች ልማት ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ ወደ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በመቀየር መዘጋጀቱን እና ተግባራዊ ለማድረግ በቅድሚያ ለክለቦች ይፋ እንደሚደረግ ጠቅሰዋል። በተጨማሪም ሁሉም ክለቦች የሴት ፊዚዮቴራፒስት መቅጠር እንደሚገባቸውና ፌዴሬሽኑ በዘንድሮ ዓመት ይህንን ተግባራዊ እንደሚያደርግ አስታውቋል።

የጨዋታዎቹን የቀጥታ ስርጭትን በተመለከተም በተሰጠ ማብራሪያም ስርጭት መኖሩ ጥቅሙ የሁሉም ቢሆንም ሥራውን ገብቶ ለመሥራት ፍላጎት ያላቸው ተቋማት አናሳ መሆኑና ፍላጎት አለማሳየታቸው ለፌዴሬሽኑ ፈተና እንደሆነበት ተጠቁሟል። ያምሆኖ የተመረጡ ጨዋታዎችን ከፌዴሬሽኑ የኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር በቀጥታ የሚተላለፉበትን ሁኔታዎች ለመፍጠር ጥረት እንደሚደረግ ታውቋል።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ